ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ረቡዕ
83ኛ ዓመት ቁጥር 107 ታኅሣሥ 17 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00
ብዕራችን ስኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ለምክክሩ ስኬታማነት
## መገናኛ ብዙኃንና ኮሚሽኑ የጋራ እቅድ አውጥተው ሲሠሩ ይገባል

**- በአማራና ትግራይ ክልሎች የተሳታፊ ልየታ እንዲጀመርም ማሳሰቢያ ተሰጥቷል**

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት መገናኛ ብዙኃንና የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የጋራ ዕቅድ አውጥተው ሊሠሩ እንደሚገባ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባዔ አቶ ታገሰ ጫፎ አስታወቁ፡፡ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በአማራና ትግራይ ክልሎች የተሳታፊ ልየታ ሊጀምር እንደሚገባ ተመላክቷል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አፈፃፀም ላይ ያደረገው የመስክ ምልከታ ሪፖርት ትናንትና ውይይት ተደርጎበታል፡፡

በወቅቱ አፈጉባዔ አቶ ታገሰ ጫፎ እንደገለጹት፤ በማህበረሰቡ ዘንድ በሚፈለገው ደረጃ ስለምክክሩ ግንዛቤ ለመፍጠር መገናኛ ብዙኃንና ኮሚሽኑ የጋራ እቅድ አውጥተው ሊሠሩ ይገባል፡፡

ሀገራዊ ምክክሩን ስኬታማ ማድረግ የሚቻለው ስለምክክሩ ዓላማ ማህበረሰቡን ማሳወቅ ሲቻል ነው ያሉት አፈጉባዔው፤ ለዚህም የመገናኛ ብዙኃን ሚና ከፍተኛ ነው

ስምክክሩ ስኬታማነት ... ወደ ገጽ4 ዞሯል


አፈጉባዔ ታገሰ ጫፎ




## የገናና የጥምቀት በዓላትን በደመቀ ሁኔታ ለማክበር ዝግጅት እየተደረገ ነው

ገጽ 4


ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

ገብረመስቀል ጫላ (ዶ/ር)

## በሰባት ዓመታት ውስጥ ከ5 ሺህ 700 በላይ ምርቶች ከቀረጥ ነፃ ይሆናሉ

**- ኢትዮጵያን የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ስማድረግ እየተሠራ ነው**

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በሰባት ዓመት ውስጥ ከአምስት ሺህ 700 በላይ ምርቶች ከቀረጥ ነጻ እንደሚሆኑ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ገለጸ፡፡ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ እስከ 2026 ድረስ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል እንድትሆን እየተሠራ

በሰባት ዓመታት ውስጥ ... ወደ ገጽ4 ዞሯል

# በአምስት ወራት ከ919 ሺህ በላይ የግብርና ሜካናይዜሽን መሣሪያዎች ከቀረጥ ነፃ ገብተዋል

**ዳግማዊትአበበ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አምስት ወራት 919 ሺህ 592 የግብርና ሜካናይዜሽን መሣሪያዎችን ከቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር እንዲገቡ ድጋፍ ማድረጉን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ሜካናይዜሽን ባለሙያ አቶ ወንድዬ ገዛኸኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለአስመጪዎች ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ማረጋገጫ በመስጠት ባለፉት አምስት ወራት ውስጥ ከ919 ሺህ በላይ የግብርና ሜካናይዜሽን መሣሪያዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ድጋፍ አድርጓል፡፡

እንደ ባለሙያው ማብራሪያ፤ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ከተደረጉ የግብርና ሜካናይዜሽን መሣሪያዎች መካከል ትራክተሮች፣ የውሃ መስኖ ፓምፖች እና ዘመናዊ የእህል ማከማቻ ቴክኖሎጂዎች ይገኙበታል፡፡

ሚኒስቴሩ ባደረገው ድጋፍ አራት ሺህ 117 ትራክተሮች ከነተቀጽላ መሣሪያዎቻቸው እና 137 ሺህ 295 የመስኖ ፓምፖች መግባታቸውን ያብራሩት ባለሙያው፤ በተጨማሪም 632 የሰብል አጭዶ መውቂያዎች እና 116 የእንስሳት መኖ ማዘጋጃ መሣሪያዎች ገብተዋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የአፈር መሸርሸርና ጨዋማነት እንዳይከሰት የሚረዱ ውሃ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች፤ 203 ሺህ 127 የነፍስ ወከፍና የትራክተር ተቀጣይ የመርጫ




ቴክኖሎጂዎች፤ 547 ሺህ 291 ዘመናዊ የእህል ማከማቻ ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም 27 ሺህ 14 እንስሳት ርባታ ቴክኖሎጂዎች እና መሣሪያዎች ወደ ሀገር እንዲገቡ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ድጋፍ አድርጓል ብለዋል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መለዋወጫዎቹ ከገቡም በኋላ የግብርና ሜካናይዜሽን ማሽነሪዎችን የአጠቃቀም ሥልጠና የሚሰጡ ባለሙያዎችን በማዘጋጀት ሥራዎች መሥራቱን አመላክተዋል፡፡

በዋናነት የሜካናይዜሽን መሣሪያዎች ተገዝተው ከገቡ በኋላ በትንሹ እስከ አስር ዓመት ማገልገል እንዲችሉ

በአምስት ወራት ከ919 ሺህል ... ወደ ገጽ4 ዞሯል






ዜና

# የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በከተሞች መካከል ጤናማ ውድድር እንዲኖር ያስችላል

**ሳሙኤል ወንደሰን**




ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በከተሞች መካከል ጤናማ የእርስ በእርስ ውድድር እንዲኖር እንደሚያስችል የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ ገለጹ። በ9ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የምርጥ ከተሞች ውድድርና ሽልማት እንደሚኖርም ገልጸዋል።

9ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም "የዘመኑ ከተሞች ለኢትዮጵያ ብልፅግና" በሚል መሪ ሃሳብ ከየካቲት 9፣ 2016 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 15፣ 2016 ዓ.ም ድረስ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ሶዶ ከተማ ይካሄዳል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ ፎረሙን አስመልክተው ትናንት በሰጡት መግለጫ እንደተናገሩት፤ ፎረሙ የከተማ ከንቲባዎች እና አመራሮች የነዋሪዎቻቸውን ችግሮች ለመፍታት በጋራ እንዲመክሩ እድል ይፈጥራል ብለዋል።

ፎረሙ ከንቲባዎች በሚመሯቸው ከተሞች በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በመኖሪያ ቤት ግንባታ እና በመሠረተ ልማት አቅርቦት ባለሀብቱን እና ኅብረተሰቡን በማሳተፍ እና ባለቤት በማድረግ ከተሞች ላይ ውጤት ለማምጣት በማሰብ የተመሠረተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ፎረሙ ከተሞችን ውብ፣ ጽዱ እና አረንጓዴ በማድረግ ለነዋሪዎች ማመቻቸት ላይ የሚሠራ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሯ፤ ድህነት ቅነሳ እና ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ ላይም አተኩሮ ይሠራል ብለዋል።

ከዚህም ባለፈ ፎረሙ በከንቲባዎች መካከል የእርስ በእርስ ትብብር እና የተሞክሮ ልውውጥ እንዲኖር እንደሚያስችል ጠቁመው፤ በከተሞች ለሚታዩ ችግሮች የተናጥል ሳይሆን የጋራ መፍትሔ ለማምጣትና የልምድ ልውውጦችን ለማድረግ እንደሚያስችል ገልጸዋል።

ፎረሙ የከተማ ከንቲባዎች ተገናኝተው በወቅታዊ የከተሞች የትኩረት አጀንዳ ላይ ጽሁፍ ቀርቦ የሚወያዩበት መሆኑን ሚኒስትሯ አስረድተዋል፡፡

ከተሻሉ አሠራሮች ልምድ የሚቀሰምበት፤ ከፈተናዎች ለመውጣት መፍትሔ የሚፈለግበት እና የተሻለ አፈጻጸም ላከናወኑ ከንቲባዎች ዕውቅና የሚሰጥበት እንደሆነም ተናግረዋል።

የድቡብ ኢትዮጵያ ክልል የከተማና መሠረተ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ብርሃኑ ዘውዴ በበኩላቸው፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አዲስ የተደራጀ ክልል እንደመሆኑ መጠን የፎረሙ መካሄድ መልካም አጋጣሚዎችን ይፈጥራል ብለዋል።

በዚህም በክልሉ ያሉ ከተሞች እንዲነቃቁና የመሠረተ ልማት ግንባታ ላይ ማከናወን ያለባቸውን ተግባራት ተሞክሮ እንዲያገኙ ያስችላል ብለዋል።

ወላይታ ሶዶ ከተማ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን ማዘጋጀቷ በክልሉ ለሚገኙ ከተሞች ተስፋ ነው ያሉት አቶ ብርሃኑ፤ ከሌሎች ከተሞች ጋር እንዴት በጥምረት መሥራት እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ ዕድል ይፈጥራል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በወላይታ ሶዶ ከተማ የሚካሄደው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በደማቅ ሁኔታ እንዲከናወን የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ ነው ያሉት ደግሞ የወላይታ ሶዶ ከተማ ከንቲባ ጀገና አይዛ ናቸው።

እንደ ከንቲባ ጀገና ገለፃ፤ ፎረሙ የሚካሄድበትን ቦታ የማዘጋጀት፣ የከተማውን ጽዳትና ውበት የመጠበቅ፣ የሰላምና ጸጥታን የማስጠበቅ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በተለይ የሕዝብ ውይይት ሥራ በማከናወን፣ የእንግዳዎች አቀባበልንና የማረፊያ ቦታዎችን የማመቻቸት፣ ከዚህ በፊት ፎረሙ የተካሄደባቸውን ከተሞች ተሞክሮ የመቅሰም ሥራ ተሠርቷል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ለተከታታይ ስምንት ዙሮች በተለያዩ ከተሞች መካሄዱ ይታወቃል።



አቶ ሀፍታይ ገብረእግዚያብሔር

# የከተማዋን የቱሪዝም ፀጋ ወደ ገቢ ለመለወጥ ጥናቶችን መሠረት ያደረገ ሥራ እየተከናወነ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የከተማዋን የቱሪዝም ፀጋ ወደ ኢኮኖሚያዊ ገቢ ለመለወጥ ጥናቶችን መሠረት ያደረገ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ባህል፤ ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ፡፡ ቢሮው በከተማዋ በቱሪዝም ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሙያዎች የቱሪዝም መረጃ አሰጣጥና ፕሮሞሽን ትናንት ሥልጠና ሰጥቷል፡፡

በቢሮው የቱሪዝም ዘርፍ ምክትል ኃላፊ አቶ ሀፍታይ ገብረእግዚያብሔር በሥልጠናው ላይ እንደገለጹት፤ ከተማዋ ከዚህ በፊት የነበሩትንና አዳዲስ የተሠሩትን ጨምሮ በርካታ የቱሪዝም ፀጋዎች አሏት፡፡

በተደረገው ጥናት መሠረት እነዚህን የቱሪዝም ሀብቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከማስተዋወቅ፤ ገበያውን ከማሳደግ እና ወደ ኢኮኖሚ ገቢ ከመለወጥ አንጻር አሁንም ክፍተቶች አሉ ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አቶ ሀፍታይ እንዳስታወቁት፤ ያለውን ሀብት በማስተዋወቅ ረገድ ከቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር በጋራ ጥናቶች ተካሂደዋል።

ጥናቶቹ የመዲናዋን የቱሪዝም ሀብት ለመለየት፣ ለማልማትና ለኢኮኖሚ ገቢ ለማዋል የሚረዱ ዝርዝር ሃሳቦች የያዙ መሆናቸውን አስረድተዋል።

ቢሮው ጥናት ላይ በተመሠረተ ሁኔታ የተለያዩ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የሚዲያ አውታሮችን እንዲሁም የተለያዩ ስብሰባዎችን ተጠቅሞ የቱሪስት መዳረሻዎችን ለማስተዋወቅ እየሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

በጥናቶቹ መሠረት በዘርፉ ያለውን የዕውቀትና ክህሎት ክፍተት ለመሙላት የተለያዩ ሥልጠናዎች እንደሚያስፈልጉ መለየቱን አመላክተዋል።

ለባለሙያዎች የተሰጠው ሥልጠናው በዘርፉ ያለውን የእውቀት ክፍተት ለመሙላት ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን ጠቁመው፤ ሥልጠናው የባለሙያው አቅም በመገንባት የቱሪስት ፍሰቱን ለመጨመር ያስችላል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የቱሪዝም ዘርፉ የትኩረት አቅጣጫ ከተሰጠባቸው አምስት የልማት ዘርፎች አንዱ መሆኑ አበረታች ጉዳይ መሆኑን አቶ ሀፍታይ ተናግረዋል፡፡

አዲስ አበባ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ከንቲባ አዳነች አቤቤ በከተማዋ ያሉ የቱሪስት መዳረሻዎች ላይ አስፈላጊውን ትኩረት ሰጥተው ድጋፍ እያደረጉ ይገኛል ብለዋል፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ባህል፤ ኪነጥበብና ቱሪዝም ፅህፈት ቤት የቅርስ ጥበቃ ባለሙያ አቶ ፋሲል ደበበ በበኩላቸው፤ ከሥልጠናው አጭርና ግልጽ በሆነ መልኩ ስለቱሪዝም ሀብትና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ግንዛቤ ማግኘታቸውን ገልጸዋል፡፡

አንድን መስህብ እንዴትና በምን አይነት መልኩ ማስተዋወቅ እንሚቻል የተሻለ ግንዛቤ ያገኙበት መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በተጨምሪም ቱሪዝም እንዳይዳከምና የተሻለ ገቢ የሚፈጥር እንዲሆን ምን አይነት ሥራዎች መሠራት አለባቸው የሚለውን መረዳት ያስቻለ ነው ሲሉ ሥለሥልጠናው ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

ሥልጠናውን ከተካፈሉ ተሳታፊዎች መካከል በኢትዮጵያ ቱር ኦፕሬተር አሶሴሽን የአባላት ጉዳይ ኃላፊ ወይዘሮ ቤዛ ጥላሁን በበኩላቸው፤ የተሰጠው ሥልጠና የቱሪዝም ሀብቶችን ጠንቅቀን እንድናውቅና ሌሎችን እንዴት ማስተዋወቅ እንደምንችል ግንዛቤ የሚሰጥ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሥልጠናው በራስ አቅም ለቱሪዝም ዕድገት ማትረፍ የሚቻለውን እና የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በአግባቡ ለመረዳት በር የከፈተ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በቱሪዝም ሚኒስቴር የፕሮሞሽንና ማርኬቲንግ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሌንሳ መኮንን ሥልጠናውን የሰጡ ሲሆን በመዲናዋ የሚገኙ የተለያዩ የቱሪዝም ባለሙያዎች ተገኝተዋል፡፡





# የከተማ ግብርና የምግብ ፍጆታ ከመሸፈን ባሻገር የገቢ ምንጭ እየሆነ ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ በከተሞች የተጀመረው የግብርና ሥራ የቤተሰብን የምግብ ፍጆታ ከመሸፈን አልፎ የገቢ ምንጭ እየሆነ መምጣቱ ተገለጸ፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በከተማ ግብርና ልምዶችና ተግዳሮቶች ዙሪያ ትኩረት ያደረገ አውደ ጥናት ትናንት አካሂዷል፡፡

የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ድሪባ ገለቲ (ዶ/ር) በአውደ ጥናቱ ላይ በሰጡት ገለጻ፤ ኢንስቲትዩቱ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ ሰፊ ጥናትና ምርምር እያከናወነ ነው፡፡

በተለይም በደጋማ አካባቢዎች በሚሠሩ ምርምሮች ደጋፊ ቴክኖሎጂዎችን በመረጃ የማውጣት፤ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎችን የመደገፍ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ በአሁኑ ወቅት እያደረገ ያለውን የከተማና ከተማ ዙሪያ ግብርናን በተመለከተ አጠቃላይ ሀገራዊ ቅኝት ሲያደርግ መቆየቱን የገለጹት ዶክተር ድሪባ፤ በጥናቱ እንደሀገር የከተማ ግብርና ሥራው ያለበትን ጠንካራ ጎንና ችግሮች መለየት እንደተቻለም ጠቁመዋል፡፡

ዘርፉ ከምግብ ፍጆታ ባሻገር የገበያ ትስስርን በመፍጠር ለሥራ እድልና ለገቢ ምንጭ እየዋለ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

የከተማና ከተማ ዙሪያ ግብርና ሥርዓት ያለበት ደረጃን ለመለየት በተደረገው ሀገራዊ ቅኝት፤ ሥራው የቤተሰብ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥና ከሥራ እድል ፈጠራ አንጻር ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከተ እንዳለ ጠቅሰዋል፡፡

የከተማ ግብርና የነዋሪዎችን የገቢ ምንጭ ከመፍጠር አኳያም ጉልህ አበርክቶ እንዳለው አመልክተዋል፡፡

በመንግሥት የልማት አቅጣጫ ተካትቶ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የከተማ ግብርና ሀገራዊ ቅርጽ ይዞ በሁሉም አካባቢዎች እየተሠራ እንዳለም ጠቅሰዋል፡፡

እንስሳት፣ አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ በከተማ ደረጃ እየተከናወኑ ያሉት የግብርና ሥራዎች ትልቅ የገቢ ምንጭ መሆናቸው በጥናቱ ተመላክቷል ብለዋል፡፡

ሥራው የቤተሰብ የምግብ ዋስትናን በመደገፍ በኩልም ሆነ የገበያ የእሴት ሰንሰለቱን ለማስፋት አስቻይ የፖሊሲ ማዕቀፍ እንዳለው ተናግረዋል፡፡

የከተማ ግብርና ሥራው የግብርና ትራንስፎርሜሽንን ከመደገፍ አኳያም ሚናው ትልቅ መሆኑን ገልጸው፤ በተደረገው ጥናት መሠረት የመዋቅር፣ የግብዓት አቅርቦትና የባለሙያ እጥረት መኖሩን አመልክተዋል፡፡

የከተማ ግብርና በአስር ዓመቱ መሪ የልማት እቅድ ውስጥ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ በመሆኑ እንደ ሀገር ዘርፉን ለማሳደግ ክፍተቱ የተስተዋለባቸው ጉዳዮች ላይ መንግሥት በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ አንስተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርና ኢኮኖሚክስ ምርምር አስተባባሪ እንደሻ ሀብቴ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የከተማ ግብርና የስራ ዕድልን እንደሚያሰፋ፣ ወጪን እንደሚቀንስ እና የገበያ ትስስርን ለመፍጠር ከፍተኛ ኦኖኮሚያዊ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸዋል፡፡

ለግብርና እንግዳ ለሆነው የህብረተሰብ ክፍልም ተጨማሪ ግንዛቤ የሚፈጥርና ሥራውን በስፋት ለማከናወን እንደሚረዳም ነው የተናገሩት፡፡

ሥራውን በማስፋት የከተማ ነዋሪዎችን ቁጥር ግምት ውስጥ ያስገባ ተደራሽነት ሊኖር እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡

የከተማ ግብርና የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ጀምሮ በርካታ ጠቀሜታ እንዳለው ጠቁመው፤ ባለ ድርሻ አካላት በዘርፉ የሚያጋጥመውን ችግር ለመፍታት በቅንጅት መሥራት እንዳለባቸውም ዶክተር እንደሻ አሳስበዋል፡፡

ዜና



አቶ መላኩ ታምሩ

# በመዲናዋ

## የሚሰጡ 11 አገልግሎቶችን ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ ሂደት ተጀምሯል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ለሶስቲኛ ወገን ሊተላለፉ ከታቀዱ 24 አገልግሎቶች መካከል 11ዱን ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ ሂደት መጀመሩን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ገለጸ።

በቢሮው የሰው ሀብት ልማት አስተዳደር ዘርፍ ኃላፊ አቶ መላኩ ታምሩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ 11 የአገልግሎት አይነቶችን ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ (የአውትሶርስ) ሂደት ተጀምሯል።

በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙና ለሶስስተኛ ወገን ተላልፈው የሚተገበሩ የአገልሎት አይነቶች 24 መሆናቸውን የገለጹት አቶ መላኩ፤ ከዚህ ውስጥ 11ዱን አውትሶርስ ለማድረግ የጨረታ ሰነድ የማዘጋጀት ተግባር በመጠናቀቁ ጨረታው በቅርቡ ይጀመራል ብለዋል።

የተለያዩ ድርጅቶች ጨረታውን ካሸነፉ አገልግሎቶቹን የሚያቀርቡበት ዝርዝር ሁኔታ እንደሚመቻች አስረድተዋል።

አቶ መላኩ እንደተናገሩት፤ ለሶስተኛ ወገን የሚተላለፉ አገልግሎቶች ከኢንዱስትሪ ልማት፣ ከስራና ክህሎት፣ ከፕላን ኮሚሽን፣ ከየመሬት ልማት አስተዳደር፣ ከመሬት ምዝገባ መስሪያ ቤቶችና በሌሎች ተቋማት የሚገኙ ናቸው።

ከዚህ በፊት አንዳንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የፅዳትና ጥበቃ ሠራተኞችን በእራሳቸው ከመቅጠር በተለየ አውትሶርስ ማድረጋቸውን በማስታወስ፤ የአገልግሎቶቹ አውትሶርስ መደረግ ነዋሪውን በስፋት ተጠቃሚ ያደርጋል ብለዋል።

የመዲናዋን አገልግሎቶቹን አውትሶርስ ማድረጉ አገልግሎቶችን በሰፊው ተደራሽ ከማድረግ በተጨማሪ የመንግሥት ተቋማት ጋር ያለውን የሥራ መጨናነቅ የሚያስቀር ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ለእንግልት የተጋለጡ የነበሩ ተገልጋዮችን በተፈለገው ቦታ ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አሠራር በመሆኑ በሰፊው ተግባራዊ እንደሚደረግ አመላክተዋል።

በአዲሱ አሠራር መሠረት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ይሠራል ያሉት አቶ መላኩ፤ ውጤታማነቱ እየተመዘነ አመርቂ ውጤት ያላመጡትን የሶስተኛ ወገን አገልግሎቶች እንዲቋረጡና በተቋማት እንዲሰጡ ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

አቶ መላኩ እንደገለጹት፤ በአሰራሩ መሠረት የበለጠ ውጤት ከተገኘበት ደግሞ የአውትሶርስ ሂደቱ እንዲስፋፋ ይደረጋል።

ስለ አውትሶርስ ሂደቱ ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ተሞክሮ ለማግኘት ጥረት እንደተደረገ ገልጸውም፤ በዚህም በምን መልኩ በመሥራት ውጤታማ መሆን ይቻላል፤ አገልግሎቶቹን በምን አይነት መልኩ ነው አውትሶርስ መደረግ ያለባቸው የሚሉ እና ሌሎች ጥያቄዎች በምሁራን ተጠንተዋል ብለዋል።

በመሆኑም በምሁራን የተጠኑትን እውቀቶች ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማስተሳሰር ተግባራዊ እንደሚደረጉ አቶ መላኩ አስታውቀዋል።

አገልግሎቶችን ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ (አውትሶርስ) አሠራር በመንግሥት የሚሰጡ አገልግሎቶች በኮንትራት ወደ ግለሰቦችና ማህበራት በማዞር ሕዝቡን የሚያገለግልበት አሠራር እንደሆነም ተገልጿል።

# በዞኑ ከበጋ ስንዴ ልማት 14 ነጥብ 9 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዷል

**ማርቆስ በላይ**



አዲስ አበባ፡- በምሥራቅ ሸዋ ዞን ከበጋ ስንዴ ልማት 14 ነጥብ 9 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት መታቀዱን የዞኑ ግብርና ጽህፈት ቤት አስታወቀ። 350 ሺህ ሄክታር መሬት በስንዴ ዘር ለመሸፈን እየተሠራ መሆኑም ተገልጿል።

የምሥራቅ ሸዋ ዞን የግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ መስፍን ተሾመ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዞኑ በበጋ ስንዴ ከሚለማው 350 ሺህ ሄክታር መሬት 14 ነጥብ 9 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዷል።

ባለፈው ዓመት በበጋ ስንዴ 204 ሺህ ሄክታር መሬት መልማት መቻሉን ያነሱት ኃላፊው፤ ከዚህም ስምንት ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል ማግኘት መቻሉን አስታውሰዋል።

በዘንድሮው ዓመት የሚለማውን መሬት በማሳደግ 14 ነጥብ 9 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዷል ብለዋል።

በዞኑ የበጋ ስንዴን 350 ሺህ ሄክታር መሬት በስንዴ ዘር ለመሸፈን እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ እስካሁን 210 ሺህ ሄክታር መሬት ታርሷል ብለዋል። ከዚህም ውስጥ 148 ሺህ ሄክታር መሬት በስንዴ ዘር መሸፈኑን ገልጸዋል።

የበጋ ስንዴ ልማት በዞኑ በሚገኙ አስራ አንድ ወረዳዎች ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን የገለጹት አቶ መስፍን፤ ወጣቶችና ሴቶችን ጨምሮ 118 ሺህ አርሶ አደሮች በስንዴ ልማቱ እየተሳተፉ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

የስንዴን ምርትና ምታማነት ለማሳደግ የአረም ቁጥጥር፣ ድጋፍና ክትትልን ጨምሮ የግብዓት አቅርቦትና ለአርሶ አደሮች ሥልጠና በስፋት እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለስንዴ ልማቱ 14 ሺህ ፓምፖች በሥራ ላይ ይሰማራሉ ብለዋል።

በዞኑ በተለያዩ የግብርናው ዘርፎች ለ70 ሺህ ወጣቶች የሥራ እድል ለመፍጠር እየተሠራ መሆኑን ገልጸውም፤ በተለይም በዶሮ፣ በዓሳ፣ በከብት ርባታን ጨምሮ በችግኝ ዝግጅትና በስንዴ ልማት ላይ ወጣቶች እየተሳተፉ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

ዞኑ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ባለፉት አምስት ዓመታት ተግባራዊ በመደረግ ላይ መሆኑን በመግለጽ፤ የምርት ሽፋንና በምርትና ምርታማነት እድገት እያሳየ መምጣቱን አስረድተዋል።

እንደ አቶ መስፍን ገለፃ፤ በዞኑ የበጋ ስንዴ ምርት በትራክተር የማረስ ሽፋን እድገት አሳይቷል። ምርትና ምርታማነቱ በቴክኖሎጂ በመታገዝ ክትትል ይደረግበታል።

የበጋ ስንዴ ምርት የአርሶ አደሮች ገቢ በማሳደግ የቁጠባ ባህል እንዲጨምር ማስቻሉን ጠቅሰው፤ በተለይም የሥራ ባህልን በመቀየር አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ማድረጉን ገልጸዋል።




# ንባብን የማረሚያ ቤቶች ባህል ማድረግ ያስፈልጋል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- ንባብን የማረሚያ ቤቶች ባህል ማድረግ እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት አገልግሎት ገለጸ፡፡

አገልግሎቱ ከፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ጋር በመተባበር በቃሊቲ ማረሚያ ቤት "በመጻሕፍት እንታረም" በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት የንባብ ቀን አውደ ውይይት ወቅት አካሂዷል፡፡

የአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ይኩኖ አምላክ መዝገቡ እንደገለጹት፤ የንባብ ጽንሰ ሃሳብ ወደ ማረሚያ ቤት መግባቱ ትልቅ ለውጥ ነው፡፡ ንባብ የአእምሮ ማበልጸጊያ እንደመሆኑ በንባብ የተለወጠ አእምሮ ብዙ ነገሮች የመለወጥ አቅም አለው፡፡

በመሆኑም ንባብን የማረሚያ ቤቶች ባህል ለማድረግና የማረሚያ ቤቶችን ቤተመጻህፍት ለማደራጀት በኮሚሽኑ እየተሠራ ያለው ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል፡፡

በዚህ ረገድ ከዚህ ቀደምም ከማረሚያ ቤቶች ጋር በርካታ ሥራዎች በትብብር ሲሠራ እንደነበር ያወሱት ዳይሬክተሩ፣ በቀጣይም የቤተመጻህፍት አገልግሎቱ ከኮሚሽኑ ጋር የሚሠራው ሥራ እንደሚቀጥል ተናግረዋል፡፡

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች የተሃድሶ ልማት ምክትል ኮሚሽነር ደስታ አስመላሽ በበኩላቸው፣ እውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈውና አስተሳሰብ የሚቀየረው በንባብ ነው ብለዋል፡፡

የማረሚያ ቤቶችን ቤተመጻህፍት የማጠናከር ሥራ ለታራሚዎች ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ጠቅሰው፤ ማረሚያ ቤቶች ለታራሚዎች የሚሰጡትን ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ጥራትና ስፋት ለመጨመር እየሠራ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ኮሚሽኑ በራሱ ከሚያከናውናቸው ተግባራት በተጨማሪ የሌሎችን መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦችን ደጋፍ የሚሻ መሆኑን ጠቅሰው፤ የትብብር ሥራዎችን በማጠናከር ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

ኮሚሽኑ ከቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት ጋር እየሠራ ያለው የትብብር ስራም የዚሁ አካል ነው ብለዋል፡፡

ኮሚሽነሩ እንዳሉት፣ የሕግ ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው ከሌላው ማኅበረሰብ በተሻለ የንባብ ጊዜ ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህም ከብቸኝነት ስሜት ወጥተው ጊዜያቸውን ከመጻሕፍት ጋር እንዲያሳልፉ፣ እውቀት እንዲሸምቱ ብሎም ከማረሚያ ቤት ውጪ ስላለው ሁኔታ እንዲረዱ በማድረግ ረገድ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

ዓለም አቀፍ የታራሚ ስምምነቶች ላይም ታራሚዎች የማንበብ መብታቸውን ሊከበር እንደሚገባና የንባብ ምቹ ሁኔታ ሊፈጠርላቸው እንደሚገባ የተደነገገ መሆኑን የጠቀሱት ኮሚሽነሩ፤ በዚህ ረገድ ኮሚሽኑም ይህንን በመተግበር የታራሚዎችን አገልግሎት ለማስፋት በቀጣይም የትብብር ሥራዎችን እንደሚያጠናክር ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት ለቃሊቲ ማረሚያ ቤት 170 ሺህ ብር የሚያወጣ የመጻሕፍት ድጋፍ ያደረገ ሲሆን፤ በአውደ ውይይቱ የተለያዩ ደራሲያን፣ ከያኒያን እና የተለያዩ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም የሕግ ታራሚዎች ተሳትፈዋል፡፡

## ዜና

# በፍትሕ ሥርዓቱ ቴክኖሎጂንና ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት እየተሠራ ነው

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- በፍትሕ ሥርዓቱ ቴክኖሎጂ እና ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም የሪፎርም ሥራዎችን ታሳቢ በማድረግ እየተሠራ መሆኑን የፌዴራል የፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

የፌዴራል የፍትሕና ሕግ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ደግፌ ቡላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የፍትሕ ዘርፉ ለበርካታ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች እና ተግዳሮቶች የተጋለጠ ነው።

በዓለም አቀፍም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚከሰቱ ሁኔታዎች በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መንገድ በዘርፉ ላይ ተጽዕኖ እያሳደሩ ነው ያሉት አምባሳደር ደግፌ፤ በመሆኑም ሥልጠናዎችና ምርምሮች ይህን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገቡ ሊሆኑ እንደሚገባ ታሳቢ በማድረግ እየተሠራበት መሆኑን አስገንዝበዋል።

እንደ አምባሳደር ደግፌ ገለፃ፤ በአሁኑ ወቅት ቴክኖሎጂን መሠረት አድርገው የሚፈፀሙ ወንጀሎች እየተበራከቱ ነው። ይህን ቀደም ብሎ በነበረው አሠራር ማስኬድና መዳኘት የሚቻል አልነበረም።

በሀገሪቱ ቴክኖሎጂን መሠረት አድርገው የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በተለመደው መንገድ ብቻ ማስተካከል ያስቸግራል ያሉት አምባሳደር ደግፌ፤ በመሆኑም ጎን ለጎን የነበረውን ሕግ የማስጠበቅ ሥራ ቴክኖሎጂን በማሳደግ ሁኔታዎች እንዲታዩ የማድረግ አዝማሚያ አለ ብለዋል።

ለአብነትም የ‹‹ፎረንሲክ›› ሥልጠና ቀደም ሲል በንድፈ ሃሳብ ላይ ብቻ ተመሥርቶ ሥልጠና ይሰጥ እንደነበር ገልጸው፤ በአሁኑ ወቅት ግን በተጨባጭ መሣሪያው ሀገር ውስጥ ገብቶ ሥልጠና እየተሰጠበት ነው ብለዋል።

በተመሳሳይ መልኩ ቀደም ሲል ማስረጃዎች ሲቀርቡ ሰዎች በአካል ቀርበው ወይንም በአካል ፍርድ ቤት ተገኝተው መሆን ነበረበት ያሉት አምባሳደሩ፤ በአሁኑ ወቅት ግን አንዳንድ ጉዳዮች ፍርድ ቤት ሲቀርቡ በድምጽ እና በቪዲዮ ሊቀርቡ እንደሚችሉ ጠቁመዋል።

በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡ ሥልጠናዎችም በዋነኛነት ትኩረት የሚያደርጉት በባለሙያዎች በሚወጡ አዳዲስ ሕጎች፣ አሠራሮችና የሚከሰቱ አዳዲስ ሁኔታዎች ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ባለሙያዎች ተግባራቸውን ከሚከሰቱ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዲያከናውኑ ማድረግ ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራም ጠቅሰዋል።

ቀደም ሲል የፌዴራል ፍትህ፤ ሕግ፣ ምርምርና ሥልጠና ኢንስቲትዩት የነበረው ተቋም የፌዴራል ፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት በሚል በአዲስ የተዋቀረ ሲሆን፤ የዳኝነት ነፃነትን ለማረጋገጥ ይረዳል በሚል እምነት በቅርቡ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሆኑ ተቋማት አንዱ መሆኑ ይታወቃል።



አምባሳደር ደግፌ ቡላ

# ለምክክሩ ስኬታማነት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ብለዋል።

ምክክሩ ስኬታማ መሆን በሚችልባቸው ሁኔታዎች፣ የቅድሚያ ቅድሚያ መሰጠት ስለሚገባቸው ጉዳዮች እና የማህበረሰቡ ግንዛቤ ፈጠራ ላይ እንዲሁም በሌሎች ጉዳዮች መገናኛ ብዙኃንና ኮሚሽኑ ዝርዝር እቅድ አውጥተው ሊሠሩ እንደሚገባ አመላክተዋል።

ሀገራዊ ምክክሩን ሙሉ ለማድረግ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች የሚወክሉ አካላትን እስከቀበሌ ድረስ በመውረድ ማሳተፍ እንደሚገባ አፈጉባዔው ገልጸው፤ በትግራይና አማራ ክልሎች ላይ የተሳታፊ ልየታና ሌሎች ሥራዎች በፍጥነት መጀመር እንዳለባቸው አሳስበዋል።

አሁን ላይ በትግራይ ክልል ያለው የሰላም ሁኔታ የተሻለ በመሆኑ ባለድርሻ አካላት ወደቦታው በመሄድ ከተሳታፊ ልየታ ጀምሮ ሌሎች ሥራዎች ሊሠሩ ይገባል ብለዋል።

በአማራ ክልል ከአመራሮች ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ውይይት አድርገናል ያሉት አፈጉባዔው፤ በክልሉ የተሳታፊ ልየታንና ሌሎች ሥራዎችን ለመጀመር አመች የሆኑ አካባቢዎችን በመለየት በፍጥነት ወደሥራ መግባት ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል።

በክልሎቹ ያለውን አንጻራዊ ሰላም በመጠቀም አመቺ በሆኑ ቦታዎች ላይ መሥራት የሚቻልባቸውን ጉዳዮች ማመቻቸት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር መስፍን አርዓያ (ፕ/ር) በበኩላቸው፤ በቋሚ ኮሚቴው ለተነሱት የተሳታፊ ልየታ፣ የሚዲያና ኮሚኒኬሽንና ሌሎች ስራዎችን በግብዓትነት ወስደን እንጠቀምባቸዋለን ብለዋል።

በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚካሄደው የምክክር ሂደት በሀገሪቱ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት በመፍጠር የተሻለችና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለማነፅ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርም አስረድተዋል።

ኮሚሽኑ የተጣለበትን ታሪካዊና ሀገራዊ ኃላፊነት ለመወጣት የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ በየወረዳው የሚገኙ 50 ተሳታፊዎች እየተለዩ መሆኑን አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ መሳፍንት ተፈራ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የሀገራዊ ምክክር ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን መገናኛ ብዙኃን መረጃዎችን ለማህበረሰቡ በወቅቱና በተገቢው መንገድ የማቀበል ሃላፊነት አለባቸው።

ኢፕድ እንደሚዲያ የተጣለበትን የሕዝብና የመንግሥትን ኃላፊነት በመወጣት ከምክክሩ የሚገኘውን ጥቅም ለማህበረሰቡ የማስገንዘብና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ድጋፍ እንዲያደርጉ ይሠራል ሲሉ አስታውቀዋል።

ሀገራዊ ምክክሩን በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎችን ለህብረተሰቡ ለማድረስ ከኮሚሽን መሥሪያ ቤቱ ጋር የጋራ እቅድ ማውጣት እንደሚገባ አመላክተዋል።

እንደ ፕሬስ ታሪክን ሰንዶ የማስቀመጥ ኃላፊነት ያለብን በመሆኑ በሀገራዊ ምክክሩ ዙሪያ ትውልድን ማስተማር የሚችል ሥራ እንሠራለን ብለዋል።

ቋሚ ኮሚቴው በአዲስ አበባ፣ በሲዳማ፣ በሐረሪ፣ በቤኒሻጉል ጉሙዝ ክልሎችና በኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በመገኘት የምክክር ኮሚሽኑ ተግባርና ሂደት ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ምልከታ ማድረጉ በቀረበው ሪፖርት ተመላክቷል።

# በሰባት ዓመታት ውስጥ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሆኑም ተጠቁሟል፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ገብረመስቀል ጫላ (ዶ/ር) ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ ለአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት ኢትዮጵያ ያቀረበችው የዕቃዎች ንግድ ዝርዝር ጸድቋል፡፡

በዚህ መሠረት ከስድስት ሺህ 800 ምርቶች ውስጥ 90 በመቶ የሚሆኑት አምስት ሺህ 700 ምርቶች በሰባት ዓመታት ውስጥ ቀረጣቸው ዜሮ ይሆናል ብለዋል።

የምርቶቹን ዝርዝር የአፍሪካ የንግድ ሚኒስትሮች ምክር ቤት በሙሉ ድምጽ ተቀብሎታል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በዚህም ኢትዮጵያ የአፍሪካን ነጻ የንግድ ቀጣና መቀላቀሏን ጠቁመዋል፡፡

ታሪፍ እየቀነሰ በሚመጣበት ጊዜ ደረጃ በደረጃ የሀገር ውስጥ ምርት ተወዳዳሪ እየሆነ መሄድ እንዳለበት ጠቁመው፤ መላው የንግዱ ማህበረሰብ፣ ሸማቹ ማህበረሰብ እና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ተገንዝቦ ዝግጅት ማድረግ እንዳለበት አመልክተዋል፡፡

በአጭር ጊዜ ውስጥም ከቀረጥ ነጻ የሙከራ ትግበራ ከአንዳንድ ሀገራት ጋር እንደሚጀመር አመልክተው፤ በልዩ ሁኔታ ሶስት በመቶ የሚሆኑ በዝርዝሩ ውስጥ እንዳይካተቱ የተያዙ ምርቶች መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ የግብርና እና የተወሰኑ የኢንዱስትሪ ምርቶች በሌሎች ሀገራት ገበያዎች ላይ ተወዳዳሪ መሆናቸውን የተናገሩት ዶክተር ገብረመስቀል፤ የንግዱ ማህበረሰብ፣ አምራቹ ሕብረተሰብ፣ የመንግሥት አካላት እና የምርምር ተቋማት ምርቶቻችን ተወዳዳሪ የሚሆኑበትን አቅም እንዲጨምር ማስቻል አለባቸው ብለዋል፡፡

ጎን ለጎንም ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ከ20 ዓመት በፊት ጥያቄ ማቅረቧን ያስታወሱት ሚኒስትሩ፤ እስከ አሁን አባል ለመሆን ጥረቶች ቢደረጉም ሳይቻል መቆየቱን ተናግረዋል።

እስከአሁን አራት ጊዜ ድርድሮች መደረጋቸውን ተናግረው፤ አሁን ላይ የድርድር ሂደቱ በከፍተኛ ትኩረት እንዲመራ መደረጉንና እንደ አውሮፓ አቆጣጠር እስከ 2026 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ አባል ለመሆን በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ተናግረዋል።

የዓለም የንግድ ድርጅት የአባልነት ድርድር እና ቀጣናዊ የንግድ ትስስሮችን በበላይነት የሚመራ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሚመራ ብሔራዊ ኮሚቴ በአዲስ መልክ በቅርቡ መቋቋሙን ገልጸው፤ ኮሚቴው አንኳር ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ያሳልፋል ተብሎ እንደሚጠበቅ ጠቁመዋል፡፡

# በአምስት ወራት...

ለአርሶ አደሩ ሥልጠና መስጠት ላይ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በተጨማሪም ትኩረት ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የሚታሰቡ ቦታዎች ላይ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ከአስመጪዎች ጋር በመሆን ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ እየተከናወነ ነው ሲሉ ነው የተናገሩት።

በተጨማሪም በፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት የተዘጋጀውን የሙያ ደረጃና ሥርዓተ ትምህርት ለማሻሻል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እየተሠራ መሆኑን አንስተዋል።

በዚህም የግብርና ሜካይዜሽን ቴክኖሎጂ ኦፕሬሽን እና ጥገና ባለሙያዎችን ለማሠልጠን ከደረጃ አንድ እስከ አራት የሙያ ደረጃ እንዲሻሻል ተደርጓል ብለዋል።

# የገናና የጥምቀት በዓላትን በደመቀ ሁኔታ ለማክበር ዝግጅት እየተደረገ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ዘንድሮ የሚከበሩትን የገናና የጥምቀት በዓላትን በደመቀ ሁኔታ ለማክበር በቂ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል ሲል የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ።

የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ስለሺ ግርማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የታህሳስ እና ጥር ወራት በርካታ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡባቸው ወቅቶች ናቸው። በተመሳሳይም የገናና የጥምቀት በዓልን ተከትሎ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ፍሰት ይጨምራል።

ሁለቱ በዓላት ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የተለያዩ ቦታዎች ላይ በስፋት የሚከበሩ መሆናቸውን ሚኒስትር ዴኤታው ጠቅሰዋል።

በዚህም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጎብኚዎች ወደ ተለያዩ ቦታዎች በመሄድ መጎብኘት እዲችሉ የቱሪስት መዳረሻዎቹ ክፍት ሆነው አገልግሎት እንዲሰጡ እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

ለአብነትም ከገና በዓል ጋር በተያያዘ ወደ ላሊበላ ከተማ በርካታ ጎብኚዎች የሚሄዱ በመሆኑ ከከተማዋ ከንቲባና ከቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ጋር ውይይት መደረጉን አንስተዋል።

ወደ አካባቢው የሚሄዱ የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎችን ለማስተናገድ በቂ ዝግጅት ማድረግ እንደተቻለም አብራርተዋል።

እንደ አቶ ስለሺ ገለጻ፤ በዓላቱ በስፋት በሚከበርባቸው ቦታዎች የትራንስፖርት ችግር እንዳይኖር እና ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር በቂ የአውሮፕላን በረራዎች እንዲኖሩ በጋራ እየተሠራ ይገኛል።

በዓላቱን ምክንያት አድርገው የሚመጡ ቱሪስቶችም አማራጭ የጉብኝት ጥቅሎች እንዲኖር እንደሚደረግ ገልጸውም፤ ይህን ለማሳካትም አስጎብኚ ድርጅቶች የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ይኖርባቸዋል ብለዋል።

ሁለቱ በዓላት በሌላው ዓለም በስፋት የማይከበሩ ናቸው። በተጨማሪም አብዛኛው የዓለም ሀገራት በአሁኑ ሰዓት አዲስ ዓመትን ተከትሎ እረፍት ላይ ይገኛሉ።

በመሆኑም ከምንጊዜውም በላይ የውጭ ቱሪስቶች ይመጣሉ ተብሎ የጠበቃል ሲሉ ገልጸው፤ በዘንድሮ የገናና ጥምቀት በዓልም በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የውጭ ጎብኚዎች ወደ ሀገሪቱ ይገባሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል።

ከጸጥታ ጋር ተያይዞ ያለውን ስጋት ለመቅረፍ ቱሪስቶች በኦንላይን መረጃ ማግኘት የሚችሉበትን የሞባይል መተግበሪያ በማልማት ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በተጨማሪም ሰዎች በአካል መረጃ ማግኘት የሚችሉበትን የመረጃ ማዕከል በቦሌ አየር ማረፊያ ተገንብቶ አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ አስገንዝበዋል።

እንደ ሀገርም የቱሪስቱን የቆይታ ጊዜ ለማራዘም በአሁኑ ሰዓት ሰፊ እድል አለ ሲሉ ገልጸው፤ የገበታ ፕሮጀክቶችም ለዚህ ዋነኞቹ ናቸው ብለዋል።

አክለውም በዓላት ምክንያት በማድረግም የዲያስፖራው ማህበረሰብ ወደ ሀገር እንዲገባ ጥሪ የሚደረግ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የወንጪ ደንዲ ሐይቅ ዘመናዊ የኢኮ-ቱሪዝም ሎጅ ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ ሀብት ተጠቅማ ከድህነት መውጣት እንደምትችል ማሳያ ነው!

ባለ ብዙ ባሕሎችና ቅርሶች መድብል ከሆነችው ኢትዮጵያ ከጥንታዊም ሆነ ከመካከለኛው ብሎም ከዘመናዊ ታሪኳ የሚቀዱ ዘርፈ ብዙ ሀብቶች አሏት። ከታሪካዊና ባሕላዊ ቅርሶቿም በተጨማሪ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ መስሕቦች ባለቤትም ነች። ይህንኑ እውነታ የተረዳው የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ተቋም (ዩኔስኮ) 16 ቅርሶቿን በመመዝገብ በአፍሪካ ግንባር ቀደም መሆኗን አረጋግጧል።

ከለውጡ ወዲህ መንግሥት አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻ ግንባታዎች በስፋት በማከናወንና እና ለቱሪዝም ዘርፉ መጠናከር የማይተካ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል። እንደ ሀገርም መንግሥት ኢኮኖሚውን ወደ ፊት ያሻግራሉ ብሎ ተስፋ ከጣለባቸው የግብርና፤ ኢንዱስትሪ፤ ማዕድንና ቴክኖሎጂ ጋር በአንድነት የቱሪዝም ዘርፉን የመሪነት ሚና እንዲኖረው አድርጓል።

ይህንኑ ሀገራዊ ርዕይ መሠረት በማድረግም ሀገራዊ ለውጡ እውን ከሆነበት 2010 ዓ/ም ጀምሮ የተፈጥሮ ሀብቶችን በማወቅ፤ በመለየት፤ በማልማትና መመጠቀም ረገድ እምርታዊ ለውጦች ታይተዋል። በአጠቃላይ ወቅቱ ለቱሪዝም ዘርፉ ትንሳኤ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

በተለይም በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሀሳብ አፍላቂነት እና መሪነት ለዘርፉ የተሰጠው ልዩ ትኩረት የሚያበረታታ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገበታ ለሸገር፤ ገበታ ለሀገር እና ገበታ ለትውልድ በሚል ማዕቀፍ በሀገራችን የሚገኙትን የቱሪዝም መዳረሻዎች በዘመናዊ መልክ እንዲለሙ እና ለቀረው ዓለም እንዲተዋወቁ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ተቀርፀው ወደ ሥራ ተገብቷል። መዲናችን አዲስ አበባን ጨምሮ በአራቱም ማዕዘናት ሀብቶችን በመለየትና በማልማት የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ እጅግ በርካታ ሥራዎች ተከውነዋል።

በገበታ ለሸገር የቱሪስት መዳረሻዎች ግንባታ የአንድነት፤ የወዳጅነት እና የእንጦጦ ፓርኮች ለአዲስ አበባ ድምቀት ሆነዋታል። ለወትሮው በቱሪስት መተላለፊያነት የምትታወቀው አዲስ አበባ የቱሪስቶች መቆያ የመሆን ዕድልም አግኝታለች። በገበታ ለሀገር ፕሮጀክትም የጎርጎራ፤ የኮይሻ እና የወንጪ የቱሪስት መዳረሻዎች ለኢትዮጵያ የቱሪዝም ዕድገት ተጨማሪ ዕድሎችን ፈጥረዋል።

የገበታ ለሀገር አካል የሆነውና በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አመንጪነት መጋቢት ወር 2013 በይፋ ግንባታው የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ከአዲስ አበባ 127 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በሚገኘው የወንጪ ደንዲ ሐይቅ ዘመናዊ የኢኮ-ቱሪዝም ሎጅ የኢትዮጵያን የቱሪዝም ዕድገት አንድ ደረጃ ከፍ የሚያደርግና ለአካባቢው ኅብረተሰብም ዘላቂ የሆነ የገቢ ምንጭ የሚፈጥር ነው።

ፕሮጀክቱ አካባቢውን በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ ልዩ የቱሪዝም መስሕብ ከማድረጉም በሻገር የኢኮኖሚያዊ ፋይዳውና የሀገሪቱን ገጽታ ከመለወጥ አንጻር ፋይዳው ትልቅ ነው። ወንጪ ደንዲ የኢኮ-ቱሪዝም ፕሮጀክት በሕዝብ ትብብር የተሠራ በመሆኑ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርግና ለ560 ሰዎችም የሥራ ዕድል የሚፈጥር ነው።

የኢኮ-ቱሪዝም ፕሮጀክቱ እስከ 39 ኢኮሎጆችና ሌሎች ተጨማሪ የመዝናኛ ስፍራዎችን ያቀፈ ነው። በፕሮጀክቱ ባለ አምስት ኮከብ ሆቴሎች፣ ባሕላዊ ሎጆና ሬስቶራንት፣ የአትሌቲክስ መንደር፣ የጎልፍ ክለብ ከመካተታቸውም ባሻገር በስፋት በአደጉት ሀገራት የሚገኙ ግዙፉ የመዝናኛና የውሃ ፓርኮችንም የያዘ ነው።

የወንጪ ደንዲ ሐይቅ ዘመናዊ የኢኮ-ቱሪዝም ሎጅ ኢትዮጵያ ያላትን ዕምቅ የተፈጥሮ ሀብቶች በአግባቡ በማወቅ፣ በመጠቀምና በመጠበቅ ለትውልድ የሚተርፍ ሥራ መሥራት እንደሚቻል ማሳያም ነው። ኢትዮጵያ እምቅ የሆነ ሀብት ያላት ሀገር በመሆኗ ከመገፋፋትና ከመጣላት ወጥተን ሀብቶቻችንን ማልማት ከቻልን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከድህነት መላቀቅ እንድምንችል የወንጪ ደንዲ ሐይቅ ዘመናዊ የኢኮ-ቱሪዝም ሎጅ አንዱ ማሳያ ሊሆን የሚችል ነው።

የወንጪ ደንዲ ሐይቅ ዘመናዊ የኢኮ-ቱሪዝም ሎጅ ሁሉ ሌሎች የቱሪዝም ሀብቶቻችንን የብልጽግናችን መሠረት እንዲሆኑ ለማስቻል ለቱሪዝም ዘርፉ እንቅፋት የሆነውን ጦርነትና ግጭት በማስወገድ ኢትዮጵያ ያላትን ዕምቅ የተፈጥሮ ሃብቶችን እንድትጠቀም ማድረግ ያስፈልጋል።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የአርሶ አደሮች ቀን መከበር ሀገራዊ ፋይዳ!

**ዘካርያስ**

በቅርቡ በአርሶ አደሮች ቀን መከበር አስፈላጊነት ላይ አንድ መድረክ ተካሂዶ ነበር። በመድረኩ ላይ የግብርና ሚኒስቴር የእርሻና ሆርቲካልቸር ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ፣ የቀድሞ የአለማያ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማኅበር እንዲሁም አሊያንስ ፎር ሳይንስ የተሰኘ ግብር ሠናይ ድርጅት አባላት እንዲሁም አርሶ አደሮች ተገኝተዋል። የአርሶ አደሮች ቀን መከበርን አስመልክቶ የተካሄደውን መድረክ ዋቢ ያደረገ መረጃ በዚህ ጋዜጣ የግብርና ዓምድ ላይ ወጥቷል።

በመድረኩም ከ1988 እስከ 2006 ለተከታታይ ዘጠኝ ዓመታት የልማት አርበኛ አርሶ አደሮች ይሸለሙ የነበረበት መድረክ ለመታወስ በቅቷል። በዚያ መድረክ ላይ የልማት ጀግና የተባሉ አርሶ አደሮች እውቅና እንዲያገኙ ይደረግ እንደነበር ይታወቃል። በርካታ የልማት አርበኛ አርሶ አደሮች ወደ ባለሀብትነት መሸጋገራቸው እየተገለጸ ይሸለሙ የነበረበት ሁኔታ እንደነበርም ይታወሳል። ያ ለአርሶ አደሮች እውቅና የሚሰጥበት ሁኔታ ሌሎች አርሶ አደሮች እንዲበረታቱ መነሳሳት እንዲፈጠርባቸው ያደርጋል የሚል እምነትም በወቅቱ ነበር።

ያ መድረክ ክፍተቶች እንደነበሩበትም የአርሶ አደሮች ቀን መከበር አስፈላጊነት ላይ የተወያየው መድረክ ለዓመታት ተካሂዶ የተቋረጠውና ብርቱ የተባሉ አርሶ አደሮች ይሸለሙበት ደካማ ጎኖች እንደነበሩበትም ተጠቁሟል። አሁን እንዲከበር የታሰበው የአርሶ አደሮች ቀን በዓል በቀደመው መድረክ አግባብ እንዲከበር የሚፈልጉ እንዳሉም በመድረኩ ታይቷል። ጠንካራውን ይዞ ደካማውን ጥሎ መድረኩን ማስቀጠል እንደሚቻል ሀሳብ ተሰጥቶበታል።

በእርግጥም የአርሶ አደሮች ቀን ቀደም ሲል የልማት ጀግኖች በሚል ይካሄድ በነበረበት መንገድም ይሁን በሌላ መከበር ይኖርበታል። ይህ ቀን ሲከበር አብረው የሚከናወኑ በርካታ ተግባሮች ስለሚኖሩ እነዚህ ተግባሮች የአርሶ አደሩን ልማት ወደፊት ሊያራምዱ፣ ችግሮቹን አውጥቶ እንዲናገር ሊያደርጉ፣ ልምድ እንዲለዋወጥ ምቹ ሁኔታ ሊፈጥሩ ስለሚችሉ የመድረኩ ወሳኝነት ጥያቄም ጥርጣሬም ውስጥ አይገባም ባይ ነኝ። ብርቱዎች የሚበረታቱበት፣ ወደኋላ የቀሩ ልምድ የሚቀስሙበት መድረክ ሊሆን ስለሚችል የቀኑ መከበር አጠያያቂ አይደለም፤፤

**የአርሶ አደሮች ቀን ቀደም ሲል የልማት ጀግኖች በሚል ይካሄድ በነበረበት መንገድም ይሁን በሌላ መከበር ይኖርበታል። ይህ ቀን ሲከበር አብረው የሚከናወኑ በርካታ ተግባሮች ስለሚኖሩ እነዚህ ተግባሮች የአርሶ አደሩን ልማት ወደፊት ሲያራምዱ፣ ችግሮቹን አውጥቶ እንዲናገር ሲያደርጉ፣ ልምድ እንዲለዋወጥ ምቹ ሁኔታ ሲፈጥሩ ስለሚችሉ የመድረኩ ወሳኝነት ጥያቄም ጥርጣሬም ውስጥ አይገባም ባይ ነኝ። ብርቱዎች የሚበረታቱበት፣ ወደኋላ የቀሩ ልምድ የሚቀስሙበት መድረክ ሲሆን ስለሚችል የቀኑ መከበር አጠያያቂ አይደለም**

የቀኑ ይከበር መድረክ ተሳታፊዎችም በእዚህ ላይ ተማምነው እንዴትና መቼ ይከበር በሚለው ላይ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ግብረ ኃይል ሰይመዋል። በዚህ ጊዜ ሊባል ባይችልም፣ የአርሶ አደሮች ቀን አርሶ አደሩን፣ ሀገሪቱ የአርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር እያደረገች ያለችውን ርብርብና እሱን ተከትሎ እየመጣ ያለውን ለውጥ በሚመጥን መልኩ ይህ እንደሚከበር እንጠብቃለን።

በዓለም አቀፍ ደረጃም፣ በሀገር ደረጃም ‹‹.... ቀን›› የሚል መጠሪያ እየተሰጣቸው የተለያዩ ጉዳዮች ይከበራሉ፤ ከቅርብ ጊዜ ደግሞ ስሙ .... ሳምንት፣ .... ወር በሚል ለሳምንት፣ ለወር የዘለቁ የተለያዩ ዘርፎች መድረኮች ሲካሄዱ ይታያል። መድረኮቹ በጉዳዩ ላይ አንዳች ግንዛቤ ሊያስጨብጡ ስለሚችሉ እኔ መኖራቸውን እደግፋለሁ ።

ከእነዚህ ጋር ተያይዞም እንደ ዓውደ ርዕይ፣ ሲምፖዚየም፣ ጉብኝትና የመሳሰሉት ልዩ ልዩ መድረኮች ይፈጠራሉ። መድረኮች ቀኑ በሚከበርለት ዘርፍ ምን ምቹ ሁኔታ እንዳለ፣ ይህን በመጠቀም በኩል ምን ያህል ርቀት መሄድ እንደተቻለ፤ ተግዳሮቶቹ ምን እንደሆኑ፣ መፍትሔዎቹ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ይመላከትባቸዋል። ባለድርሻዎች ይገናኛሉ፤ ልምድ ይለዋወጣሉ፤ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ይካሄዳል።

መከበር ፋይዳው ከዚህም ያለፈ ሊሆን ይችላል። በእዚህ አይነቱ መድረክ አጀንዳው ደብዝዞ የነበረ ጉዳይን ማነቃቃት፣ አዲስ የተቀረጸ አጀንዳ መነጋገሪያ ማድረግ ይቻላል፤ የተረሳውን ማስታወስ፣ በቀጣይ ለሚሠራው ሥራ አቅም ማግኛ መንገድ ይፈጠራል። ከዚህ የተነሳ አርሶ አደሩ ቀን ያስፈልገዋል የሚል እምነት አለኝ። የአርሶ አደሮች ቀን እንደሚመጣ ተስፋ አደርጋለሁ ።

በዚህ መድረክ ላይ ጠቆም የተደረገው የአርሶ አደሮች ማኅበር አስፈላጊነት ነው። ጉዳዩ የበለጠ ትኩረቴን ስቦታል። ጉዳዩ በመድረኩ መነሳቱን ስሰማ በወታደራዊው መንግሥት ዘመን /በደርግ ዘመን/ የነበረው የመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበር /መኢገማ/ አስታወሰኝ። በሌ መንገድ ወደ ፍላሚንጎ አካባቢ ማኅበሩ ያሠራው በዘመኑ ግዙፍ የተባለ ሕንጻም ነበረው።

ካስታወስኩ አልቀረ አንዳንድ ነገሮችንም ላስታውስ። በዚያ ዘመን መኢገማ ብቻ ሳይሆን ሌሎች በርካታ ማኅበራትም ነበሩ። የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር /መኢሠማ/፣ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወጣቶች ማኅበር /አኢወማ/፣ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበር /አኢሴማ/፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር /ኢመማ/ የሚሉና ሌሎች በርካታ ማኅበራትም ነበሩ።

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ተጠየቅ

# ‹‹በሀገራችን ቴክኖሎጂን መሠረት አድርገው የሚፈፀሙ ወንጀሎች፤ በሰው አዕምሮ ብቻ ማስተካከል ያስቸግራል››

**- አምባሳደር ደግፌ ቡላ**
**የፌዴራል የፍትሕና ሕግ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር**

ክፍለዮሐንስ አንበርብር



**የፌዴራል ፍትሕና ሕግ ኢንስቲትዩት፤ የዳኝነት ነፃነትን እንዲረጋገጥ ለማስቻል የተቋቋመ ሲሆን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሆኑ ተቋማት መካከል አንዱ ነው። በቀጣይ የሚስተካከሉ ጉዳዮች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በርካታ የሪፎርም ሥራዎችን ማከናወኑን የሚናገረው ተቋሙ፤ ከማስረጃ አቀራረብ እና ጥናቶችም አኳያ አሁን ላይ ቀደም ሲል ከነበረው አሠራር እየተሻሻለ ስለመሆኑም ይነገራል።**

**በተለይም ቴክኖሎጂው የፍትሕ ሥርዓት አሰጣጡን ጥሉ እንዳይሄድና በቴክኖሎጂ ተደግፈው የሚሠሩ ወንጀሎችን በብቃት በመመርመር ፍትሕ ለመስጠት የሚያስችሉ ሥራዎች በትኩረት እየተከናወኑ ነው። ይህን ለማሻሻል ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የተናበበ ግንኙነት መፍጠሩንና ከሀገር ውጭ ከሚገኙ አቻ ተቋማት ጋርም በተመሳሳይ መልኩ የሚከናወኑ አበረታች ተግባራት መኖራቸውን ይገለፃል።**

**በሌላ በኩል በቂ ባለሙያ ለመሳብና ለማቆየት አለመቻል፣ የሚጠኑ ጥናቶች በተግባር ላይ ያለመዋል፣ የምርምርና የማሠልጠን አቅም ያለመዳበር፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂና መሠረተ ልማቶች ያለመሟላት እና መሰል ችግሮች ደግሞ ተቋሙን እየተፈታኑት ያሉ ተግዳሮቶች ናቸው። እነዚህንና ሌሎች መሰል ጉዳዮችን በተመለከተ የዝግጅት ክፍላችን ከኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ደግፌ ቡላ ጋር ቆይታ አድርጓል።**

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ ቀደም ሲል የነበረውን ስያሜ ከመቀየር በዘለለ በተግባር የተለወጡ የሪፎርም ሥራዎች ምንድን ናቸው?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** ተቋማችን በአሁኑ ወቅት መጠሪያው የፌዴራል ፍትሕና ሕግ ኢንስቲትዩት ነው። ቀደም ሲል የነበረው ስያሜ ደግሞ የፌዴራል ፍትሕ፤ ሕግ፣ ምርምርና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ነበር። በእርግጥ የስያሜ ለውጥ የተደረገበት ዓቢይ ምክንያት የተቋቋመበትን ዓላማ የበለጠ ይገልጻል በሚል እምነት ነው። ዋናው ቁም ነገር የስያሜ መለዋወጥ ሳይሆን ኢንስቲተዩቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ምን ምን ተግባራት እያከናወነ ነው? የተከናወኑ ተግባራትስ ምን ወጤት አስገኙ? የሚለው ነው።

ከዚህ አንፃር ሲታይ ኢንስቲትዩቱ ቀደም ሲል ሁለት ተቋም ነበር። የዳኞችና ፍትሕ አካላት ማሠልጠኛ ለብቻው፤ የጥናትና ምርምሩም ለብቻ ነበር። ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ነው የተዋሐዱት። የመዋሐዱ ዓላማው እርስ በእርሳቸው እንዲደጋገፉ ታስቦ ነው። ይህ ማለት ሥልጠና ላይ የሚታዩ ክፍተቶች በጥናትና ምርምሮች እንዲደገፉ ለማድረግ ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ የሪፎርሙ አካል ነው?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** የሪፎርም ሥራዎችን በተመለከተ ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል። ምንም እንኳን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ጥናቶችን ያከናወነ ቢሆንም በዋናነት በጥናትና ምርምር ላይ ተመስርቶ የመወሰን ልምድ በአግባቡ የዳበረ አልነበረም። ይሁን እንጂ ይህን ለማሻሻልና አዳዲስ ሕጎችን ለማውጣት ወይም ለሪፎርም ሥራዎች በግብዓትነት አገልግለዋል።

ለአብነት ያህል የወንጀል ሕግ፣ የቤተሰብ ሕግ፣ በቅርቡ የወጣው የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት ሕግ፣ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ረቂቅ፣ አዲሱ የንግድ ሕግ፣ እንዲሁም በቅርቡ የመንግሥትና ሃይማኖት ግንኙነትን በተመለከተ ጥናት ተከናውኗል።

የመንግሥትና ሃይማኖት ግንኙነትን በተመለከተ ወደፊት ፖሊሲ እንዲወጣ ስለሚፈለግ ይህን መሠረት በማድረግ በርካታ ጥናቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። ይህ ጥናት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሪፎርሙን ሥራ ለማገዝ ነው።

ከአደረጃጀት አኳያ የተበታተኑ ሥራዎችን ወደ አንድ የማምጣት ሥራ የተከናወነ ሲሆን፤ ቀደም ሲል ጥናትና ምርምሩ የተበታተነ ነበር። በአሁኑ ወቅት መዋቅሩን የማሻሻል ሥራዎች ተሠርተዋል። በፍርድ ቤቶች፣ በዓቃቤ ሕግ፣ እና ሌሎችም የሪፎርም ሥራ ድጋፍ እናደርጋለን።

ይህንና ሌሎች ተዛማጅ ጥናቶችን መነሻ በማድረግ ሕግ የማርቀቅ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል። የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ሥራዎች የሚገኙበትን ደረጃና ማሻሻያውን ለማጠናከር እና ለወደፊቱ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች በተመለከተ የዳሰሳ ጥናት ተከናውኖ ከመፍትሔ ሐሳብ ጋር ለመንግሥትና ለሚመለከታቸው ተቋማት ተላልፏል።

በፍትሕ አካላት የሚታየውን የመልካም አስተዳደር ችግር አስመልክቶ በተከናወነው ጥናት መነሻነት በፍትሕ ዘርፉ ላይ በአዲስ መልክ የሪፎርም ሥራዎችን ለማካሄድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመራ የሪፎርም ሥራ ለማከናወን የዝግጅት ሥራ ተጀምሯል።

ከዚህም በተጨማሪ የሕግ ትምህርትን ሪፎርም ጨምሮ የፍትሕ ዘርፉን ሪፎርም የማስተባበር ሥራ እንዲሁም ለፍትሕ ዘርፉ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን የማደራጀት እና ለአጠቃቀም ዝግጁ የማድረግ ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛሉ። ለፍትሕ አካላት በዕውቀቱ፣ በክህሎቱ፣ በአመለካከቱ፣ እንዲሁም በሥነ ምግባሩ ብቁ የሆነና የተሟላ ስብዕና ያለው አመራርና ባለሙያ ለማፍራት በፌደራል እና በክልል የሚገኙ በርካታ ባለሙያዎች የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች እንዲያገኙ በማድረግ ላይ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን፡- የመንግሥት እና ሃይማኖትን ግንኙነት በተመለከተ ወደፊት ፖሊሲ እንዲወጣ ስለሚፈለግ ይህን መሠረት በማድረግ በርካታ ጥናቶች ሲደረጉ መቆየታቸውን ገልጸዋል። ይህ ሃይማኖትና መንግሥት የተለያዩ ናቸው የሚለው እሳቤ ምን ያክል ያገናዘበ ነው?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** በሕገ መንግሥቱ ላይ እንደተቀመጠው ሃይማኖትና መንግሥት የተለያዩ ናቸው። አንዱ በሌላኛው ጣልቃ አይገባም። ይሁንና ይህን በተመለከተ እስካሁን ድረስ የሕግ ወይንም የአፈፃፀም ፖሊሲ አልወጣም። ነገር ግን ይህን ጉዳይ በተመለከተና በሀገራችን ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከት አንዳንድ የሚታዩ ነገሮች አሉ። ቀደም መንግሥት በሃይማኖቶች ጉዳይ ጣልቃ ይገባ ነበር። ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ ይገባ ነበር። ይህን የመደበላለቅ ሁኔታ መልክ ለማስያዝ አስፈላጊው ጥናት መካሄድ አለበት የሚል ሃሳብ በመንግሥት በኩል የተሰጠ አቅጣጫ ነበር። ይህን መሠረት አድርጎ የተሠራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ጥናቱ ከብዝኃነት አኳያ ሲመዘን ምን ይመስል ነበር?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** ይህን መሠረት በማድረግ 11 ምሑራን የተሳተፉበት ጥናት እንዲካሄድ ተደርጓል። በዚህ ጥናት ውስጥ የተለያዩ ምሑራን ተሳትፈዋል። ከእነኝህ መካከል በሃይማኖትና ሥነ-መለኮት ዙሪያ ጥናት ያካሄዱ፤ በታሪክና ሌሎችም ብቃትና ችሎታ ያላቸው እንዲሁም ሌሎች ከጥናቱ ጋር የተገናኙ ምሑራን ተሳትፈውበታል።

ጥናቱ ሀገራዊ በመሆኑም የሃይማኖት ተቋማትም እንዲሳተፉበት ተደርጓል። በሀገሪቱ የሚገኙ የተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎችም ከፍተኛ ተሳትፎ ነበራቸው። በመሆኑም ጥናቱ በርካታ ሐሳቦች እንዲካተቱበት አስችሏል።

በሌላ መልኩ ደግሞ ጥናቱን የተሻለ ለማድረግ በዘርፉ ጥሩ ተሞክሮ ያላቸው ሀገራትን አሠራርን ለማየት ተሞክሯል። ለአብነትም የፈረንሳይ፣ ጀርመን እና ሌሎች ከኢትዮጵያ ጋር ቅርበት ያላቸው ሀገራት ተሞክሮ ለመቀመር ተሞክሯል። ጥናቱ ተደርጎ በአሁኑ ወቅት ‹‹ቫሊዴሽን ወርክሾፕ›› ተደርጎ የጥናቱ ውጤት ለፍትሕ ሚኒስቴር ተልኳል።

ሚኒስቴሩ ሕግ የማርቀቅ ኃላፊነትም ስላለው ይህን ጥናት መሠረት በማድረግ ፖሊሲ ያዘጋጃሉ፤ ፖሊሲውን መሠረት በማድረግም ሕግ ይወጣል። ከዚህ አኳያ የተደረገው ጥናት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሃይማኖትና መንግሥት ጎራ መደበላለቅ ለማስወገድና ድንበሩን ለማወቅና በጋራ የሚሠሩባቸውን ጉዳዮችም በደንብን ለመለየት የሚያስችል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከኢንስቲትዩቱ ዓላማ አኳያ የሕግ ምርምሮችና ሥልጠናዎች የትኩረት ነጥቦች መሆናቸው ይታወቃል። ከዚህ አኳያ በተጨባጭ የተገኙ ለውጦች ምንድን ናቸው። ጥናቶች ተደርገዋል? ካሉ ምን ያመላክታሉ?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** ከፍ ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው የተከናወኑ ምርምሮች ለሕግ ማሻሻያና አዳዲስ ሕጎችን ለማውጣት እንዲሁም በፍትሕ ዘርፉ ለሚከናወኑ የሪፎርም ሥራዎች በግብዓትነት የዋሉበት ሁኔታ አለ። ከዚህ ሌላ ምንም እንኳን በሚፈለገው ልክ ሥራ ላይ ያልዋሉ ቢሆንም የፍትሕ ተቋማትን ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸው ምን እንደሆነ ግንዛቤ እንዲኖርና ዘርፉን የማሻሻል ሥራ ትኩረት እንዲያገኝ እገዛ አድርገዋል።

የተደረጉ ግምገማዎች እንደሚያመላክቱት፤ የተከናወኑት ጥናቶች የፍትሕ አካላትን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ ረገድ አበረታች ውጤቶች አስገኝተዋል። ሆኖም የተደረጉት ጥረቶች የሚጠበቀውን ያህል ውጤት አላስገኙም።

አሁንም የፍትሕ አካላቱ ያልተሻገሯቸው በርካታ ችግሮች እንዳሉና እነዚህን ችግሮች ለማቃለል ሥራዎችን ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑን ያሳያሉ። የሚሰጡ ሥልጠናዎችን በተመለከተ በቅርቡ በተደረገ የዳሰሳ ጥናት ሥልጠናዎች የፍትሕ ተቋማቱን ባለሙያዎች አቅም ለማሳደግ ብሎም ተቋማቱ ወጤታማ እንዲሆኑ ከፍተኛ ድጋፍ አድርገዋል። ሆኖም የበለጠ መጠናከር እንዳለባቸው አመላክተዋል። ሌሎች ሥራዎችም እንዲሁ ተጠናክረው መቀጠል ያለባቸው ናቸው።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## ‹‹በሀገራችን ቴክኖሎጂን መሠረት...

ከገጽ 6 የዞረ



**አዲስ ዘመን፡- ኢንስቲትዩቱ በርካታ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሥልጠና እንደሚሰጥ ይታወቃል። ይሁንና የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ፣ የንግድ ሕግና የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጎች በዓለማችን ላይ በየጊዜው ከቴክኖሎጂ መበራከትና መፈጠር ጋር በተያያዘ ተለዋዋጭ እየሆኑ ነው። በዚህ ረገድም ሀገራት ለትግበራም እየተፈተኑ ነው። ኢትዮጵያስ?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** የፍትሕ ዘርፉ ለበርካታ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችና ተግዳሮቶች የተጋለጠ ነው። በዓለም አቀፍም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚከሰቱ ሁኔታዎች በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መንገድ በዘርፉ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። በመሆኑም ሥልጠናዎች ይህን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገቡ ሊሆኑ ይገባል።

በአሁኑ ወቅት ቴክኖሎጂን መሠረት አድርገው የሚከሰቱ ወንጀሎች እየተበራከቱ ነው። ይህን ቀደም ብሎ በነበረው አሠራር ማስኬድና መዳኘት የሚቻል አይደለም። በሀገራችን ቴክኖሎጂን መሠረት አድርገው የሚፈፀሙ ወንጀሎች በሰው አዕምሮ ብቻ ማስተካከል ያስቸግራል። በመሆኑም የነበረውን ሕግ ከማስጠበቅ ጎን ለጎን ቴክኖሎጂን በመጠቀም የተቋሙን ሥራዎች ለመደገፍ እየተሠራ ነው። ለአብነት እኛ ዘንድ በአሁኑ ወቅት የሚሰጥ ‹‹ፎረንሲክ›› ሥልጠና አለ። ቀደም ሲል ይህ የሚታወቀው በቲዮሪ ነው። በአሁኑ ወቅት ግን በተጨባጭ መሣሪያው ሀገር ውስጥ ገብቶ በዚህ ላይ ሥልጠና ይሰጣል።

ቀደም ሲል ማስረጃዎች ሲቀርቡ ሰዎች በአካል ቀርበው ወይንም በአካል ፍርድ ቤት ተገኝተው መሆን ነበረበት። በአሁኑ ወቅት ግን አንዳንድ ጉዳዮች ፍርድ ቤት ሲቀርቡ በድምፅ እና በቪዲዮ ሊቀርቡ ይችላሉ። ስለዚህ በቴክኖሎጂ የተደገፉ ሥራዎችን የመሥራት ሁኔታዎች አሉ። አሠራራችን ከማስተካከል አኳያ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

እንግዲህ በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በዋነኛነት ትኩረት የሚያደርጉት አዳዲስ በሚወጡ ሕጎች፣ አሠራሮችና የሚከሰቱ ሁኔታዎች ላይ ባለሙያዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ተግባራቸውን ከሚከሰቱ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዲያከናውኑ ማድረግ ላይ ነው። ለዚህም ሲባል የሥልጠና ካሪኩለሞች በየጊዜው እየተፈተሹ ወቅታዊ ይደረጋሉ። አሁን ባለው ሁኔታ ቀደም ሲል ከነበሩ ሁኔታዎች የተሻሻሉ አሠራሮች እየተተገበሩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ሀገር ከንጉሡ ዘመን ጀምሮ አሁንም ድረስ የሚተገበሩ የፍትሐብሔርና መሰል ሕጎች አሉ። እንደ ኢንስቲትዩት ለመንግሥት የምታቀርቡት ምክረ ሐሳብ ምንድን ነው?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** ከተቋቋምንባቸው ዓላማዎች አንዱ የሕግ ማሻሻያ ጥናቶችን ማካሄድ እንደመሆኑ መጠን ትኩረት ከተሰጣቸው ሕጎች አንዱ የፍትሐብሔር ሕግ ነው። በዚህም መሠረት ሕጉን ለማሻሻል እና ከወቅታዊው የሀገሪቱ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም የሚረዳ ጥናት አከናውኖ የማሻሻያ ምክረ ሃሳቦችን ለሚመለከተው አካል ልኳል። በቀጣይም ሌሎችን ሕጎች ለማሻሻል እና አዳዲስ ሕጎችን ለማውጣት የሚረዱ ጥናቶችን የሚያከናውን ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ ዘመኑ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ጭምር ነው። ከዚህ አኳያ አሁን የሚሰጡ ሥልጠናዎችስ ዘመኑን የዋጁ ናቸው?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** ተቋማችን በሦስት ጉዳዮች ላይ አተኩሮ ሥልጠና ይሰጣል። የመጀመሪያው የቅድመ ሥራ ሥልጠና ሲሆን፤ አንድ የሕግ ባለሙያ ከዩኒቨርሲቲ ወጥቶ በቀጥታ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ለስድስት ወይንም ለዘጠኝ ወራት ሥልጠና ይወስዳል። ይህ ማለት ዩኒቨርሲቲ በቲዮሪ የተማሩትን በተግባር እንዲሚገ ያስችለዋል።

ሁለተኛው የሥራ ላይ ሥልጠና ነው። ይህ ማለት ደግሞ ተቀጥረው የሚሠሩ ባለሙያዎች ክህሎታቸውንና አቅማቸውን እንዲያሻሽሉ ሥልጠናዎችን ያገኛሉ። ሦስተኛው ልዩ ሥልጠና ሲሆን፤ በተለያዩ ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ የሕግ ባለሙያዎች፣ ጠበቃዎችና ነገረ ፈጆችን የማሠልጠን ጉዳይ ነው። ከዚህ አኳያ ተቋማችን ስንመለከት በዓለም ላይ ካሉት ሀገራት ደረጃ ላይ አልደረሰንም።

ከቴክኖሎጂ አኳያ እኛ በርካታ ጥረቶችን እያደረግን ነው። በእርግጥ ቴክኖሎጂ እንዳይቀድመን ስጋት አለን። የአርቴፊሻል ኢንተለጀንሱን ስንመለከት አሁን ሰው ብዙ ሳያነብ በቀላሉ መረጃ የሚያገኝበት ዘመን ነው። ይህን ከእኛ ሁኔታ ጋር ለማናበብ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠዋል። አንዳንድ ጊዜ ባለጉዳዮች በአካል ሳይገኙ በኦንላይን ዳኝነት የሚሰጥበት ጊዜ ላይ ነን። ከዚህ አኳያ በጣም ብዙ ይቀራል። በዚህ ዙሪያ በደንብ ልንሠራ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- የፍትህ ሥርዓቱን የበለጠ ለማጠናከር እና በተማረ የሰው ኃይል የተገነባ በማድረግ ረገድ ዩኒቨርሲቲዎች የላቀ ሚናቸው አላቸው። ከዚህ አኳያ ኢንስቲትዩቱ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ምን እየሠራ ነው?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** ተቋማችን በፍትሕ ላይ ይሠራል። አሁን በውስጥ አቅም ከምንሠራው ውጭ ሌሎች አማራጮችን እንመለከታለን። ሀገራዊ ጠቀሜታ ያላቸው፤ ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ትኩረት እናደርጋለን። ተቋማችን ሙሉ ለሙሉ በቂ ባለሙያ የለውም። በመሆኑም አወዳድረን ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር አብረን እንሠራለን። በተለይም ጥናትና ምርምር ላይ ዩኒቨርሲቲዎች ይሳተፋሉ። ሌላው ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በጋራ ኮንፈረንስ እናዘጋጃለን። ለምሳሌ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በሕግ መዝገበ ቃላት ላይ አብረን እየሠራን ነው።

በተጨማሪም ከሌሎች ተቋማት ጋር አብረን እንሠራለን። በአጠቃላይ በሀገር ውስጥ በክልል ከሚገኙ የምርምር እና ሥልጠና ተቋማት፣ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች እና ሌሎች የፍትሕ ተቋማት፤ እንዲሁም ከተወሰኑ የውጭ ተቋማት ጋር በጋራ የሚሠራበት ሁኔታ አለ። እነዚህ ግንኙነቶች በጋራ ጉዳዮች ላይ አብሮ ለመሥራት ፤ልምድና መረጃ ለመለዋወጥ እና ለመደጋገፍ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል።

የውጭ ሀገራትን ልምድ በተመለከተ ብዙ አልገፋንበትም። በተወሰነ ደረጃ ከኬንያ እና አሜሪካ ጋር ከሚገኝ አንድ ድርጅት ጋር ልምድ ልውውጥ እናደርጋለን። ሌላው አውሮፓ ከሚገኘውና ‹‹ሂል›› ከሚሰኝ ድርጅት ጋርም ማኅበረሰቡን ማዕከል ያደረገ ፍትሕ የሚል ጥናት አብረን እየሠራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በጥናቱ የተለዩት የፍትሕ ችግሮች ምንድን ናቸው?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** ሦስት ጉዳዮችን ለይተናል። አንደኛው መሬት ጋር በተያያዘ ያለው ነው። መሬት ላይ በርካታ ችግሮች ይስተዋላሉ። ፍርድ ቤትም በብዛት የሚመጡ ጉዳዮች ከመሬት ጋር የተያያዙ ናቸው። ሌላው ከጎረቤት ጋር ያለው ግጭት ነው። ይህ በገጠርም በከተማው ማኅበረሰብ የሚስተዋል ነው። ሦስተኛው የተደራጀ ወንጀል ነው።

ከእነዚህ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ችግሮችን ለመቀነስ አውሮፓ ከሚገኝ መንግሥታዊ ካልሆነ ድርጅት ጋር እየሠራን ነው። የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮም እያመጣን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከ‹‹ሂል›› ጋር በተደረገው ጥናት የመሬት፣ የማኅበረሰባዊ እሴት መሸርሸር ወይንም የጎረቤት ግጭትና የተደራጁ ወንጀሎችን የተመለከተው ነው። ጥናቱ ምን የሚያመለክተው ነገር አለ?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** ‹‹ሂል›› ጥናቱን ያከናወነው በራሱ ተነሳሽነት ነው። ይህ ድርጅት መሰል ጥናቶችን ከኢትዮጵያ ባለፈ በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ማለትም በዑጋንዳ፣ ኬኒያ እና ናይጄሪያ እና ሌሎች ሀገራትም አከናውኗል። በአሜሪካም ይህን ጥናት ያካሂዳሉ። ከእኛ ጋርም ሥምምነት አድርገው ጥናት የጀመሩት የቀድሞ ፍትሕ ሚኒስትር ጀኔቫ ሄደው ተፈራርመው ስለነበር ነው። የእኛ ተቋም ደግሞ ሥራውን ያስተባብራል። ጥናቱም ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የተካሄደ ነው።

ኢትዮጵያ በየዓመቱ ወደ ፍርድ ቤት ከሚቀርቡ 7ነጥብ4 ሚሊዮን ጉዳዮች መካከል እልባት የሚሰጣቸው 2ነጥብ2 ሚሊዮን ጉዳዮች ብቻ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጉዳዮችን ወደ ፍርድ ቤት አለመውሰድና በሽምግልና የመጨረስ ሁኔታ አለ። ወደ ፍርድ ቤት የሚመጣው ጉዳይ በጣም አነስተኛ ነው። 7ነጥብ4 ሚሊዮን ጉዳዮች ወደ ፍርድ ቤት መምጣታቸው ብዙ ጉዳዮች መኖራቸውን ያሳያል። ይህ ጥናት ሲካሄድ ሦስት ወርክሾፖች ኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄዱ ሲሆን፤ የተለያዩ አካላትም ተሳትፈውበታል። ጥናቱን መሠረት በማድረግም ተጨምቀው የወጡ ጉዳዮች ደግሞ ሦስቱ ጉዳዮች ናቸው።

በአሁኑ ወቅት ፓይለት ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ ነው። ይህም እነዚህን ችግሮች ለማስተካከል ምን መደረግ አለበት? የሚለውን ለማየትና በተወሰነ ቦታ ሞክሮ ለማዳበር ነው። በአጠቃላይ ሲታይ ጥናቱ ተጠናቋል፤ የሚቀረው ትግበራው ነው። በዚህ ከተሠራበት የኢትዮጵያን የፍትሕ ችግር ማቃለል ይቻላል የሚል ተስፋም አለ።

**አዲስ ዘመን፡- አሁናዊ የሀገሪቱ ሁኔታ እና የተቋሙ ሥራዎች ምን ያክል ተናበዋል ማለት ይቻላል?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** ኢንስቲትዩቱ የሚያከናውናቸው ተግባራት በመንግሥት የትኩረት አቅጣጫ እና በኅብረተሰቡ ወቅታዊ የፍትሕ ፍላጎት ላይ ያተኮሩ ናቸው። ችግሮችንና ክፍተቶችንም በሚገባ የሚለይ ነው። ሆኖም በሀገራችን ትኩረት የሚፈልጉ በርካታ የፍትሕና ሕግ ጉዳዮች ከመኖራቸው ጋር ተያይዞ ከተቋሙ አቅም አኳያ ሲታይ ለሚስተዋሉት ችግሮች እና ፍላጎቶች የተሟላ ምላሽ ለመስጠት በሚያችልበት ቁመና ላይ ነው ለማለት አይቻልም።

**አዲስ ዘመን፡-በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የሕግ መዝገበ ቃላት ለማዘጋጀት የሚያስችል 10 ሚሊዮን ብር ሥምምነት በ2013 ዓ.ም ተፈርሞ ነበር። ይህ ሥራ ከምን ደረሰ?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** በእኛ በኩል በዳኞችና በፍትሕ በኩል የሚታዩ ችግሮችን ለማቃለል ተቋማችን ጥናት አድርጓል። ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ስንመለከት የፍርድ አጻጻፍንና አተረጓጎምን ጨምሮ ችግሮች መኖራቸውን ለይተናል። ወደ ተቋማችን መጥተው ሥልጠና የሚወስዱ አሉ። የእነርሱንም ጉድለት ተመልክተን ለይተናል። በዚህ ላይ የተረዳነው በቃላት ትርጉም ጭምር ልዩነቶች መኖራቸውን ነው። ተገልጋዮች ወይንም ባለጉዳዮችም በፍርድ ቤት በሚሰጡ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የጠራ ግንዛቤ የላቸውም።

ይህን ስናይ በሀገሪቱ ያለው የሕግ መዝገበ ቃላት ችግር ስለፈጠረ ለመጀመሪያ ጊዜ የአማርኛ የሕግ መዝገበ ቃላት እንዲዘጋጅ ነው የተወሰነው። የመዝገበ ቃላቱ ሥራ የተቃና እንዲሆን አግባብነት ያላቸውን ባለሙያዎችን በማሳተፍ እየተሠራ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት ሥራው በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

መዝገበ ቃላቱ ከአማርኛ በተጨማሪም አቅም በፈቀደ መጠን በኦሮምኛ፣ ሶማሌኛ፣ ትግርኛ እና ሌሎች ቋንቋዎች የሚዘጋጅ ነው። በአሁኑ ወቅት መዝገበ ቃላቱ ተዘጋጅቶ ለገምጋሚዎች ቀርቦ የታየ ሲሆን፤ የሚቀረው ከገምጋሚዎች በተሰጠው ሐሳብ መሠረት የማስተካከልና የማጠናቀቅ ሥራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ አሁን ለሚያከናውናቸው ተግባራት ፈተናዎች ምንድን ናቸው፤ እንደ መፍትሔ የተቀመጠውስ ምንድን ነው?**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** ተቋሙ ዋናው ችግር የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት በሚችልበት ደረጃ ላይ ያለመሆኑ ነው። ለዚህም በምክንያትነት ከሚጠቀሱት መካከል በቂ ባለሙያ ለመሳብና ለማቆየት አለመቻል፣ የሚጠኑ ጥናቶች በተግባር ላይ ያለመዋል፣ የምርምርና የማሠልጠን አቅም ያለመዳብር፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂና ሌሎች መሠረተ ልማቶች ያለመሟላት ናቸው።

ተቋሙን ለማጠናከር በቅርቡ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ ተደርጓል። በተለይ የምርምር ክፍሉ ደረጃው ከፍ ብሎ ተደራጅቷል። ሌሎችም የሥራ ዘርፎች እንዲሁ በአዲስ መልክ ተደራጅተዋል። የበለጠ ውጤታማ ይሆናል በሚል እምነትም ተጠሪነቱ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲሆን ተደርጎ የማቋቋሚያ ሕጉን የማሻሻል ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል። የሕጉን ማሻሻያ ተከትሎም አደረጃጀቱንና አስተዳደሩን የማስተካከል ሥራ የሚከናወን ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ስለነበረዎት ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**አምባሳደር ደግፌ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የአርሶ አደሮች ቀን መከበር...

ከገጽ 5 የዞረ

ከእነዚህ ማኅበራት አንዳንዶቹ በኢሕአዴግ ዘመንም የሆነ ለውጥ እየተደረገባቸው ቀጥለዋል፤ የያኔው መኢሠማ የዛሬው ኢሠማኮ ለእዚህ በአብነት ይጠቀሳል። አሁንም ድረስ ከእነስማቸው የሚሠሩም አሉ። ኢሕአዴግ እንደ ዘጋቸው የቀሩ በርካታ ማኅበራት እንዳሉም ይታወቃል። ከእነዚህ ማኅበራት አንዱ ኢሕአዴግ እንደዘጋው ሳይከፍተው ያሸለበበት የመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበር /መኢገማ/ ነው።

በማኅበሩ መዘጋት ሳቢያ ኢሕአዴግ ሀገሪቱን ከተቆጣጠረ አንስቶ አርሶ አደሩ ድምፁን የሚያሰማለት፣ ስለመብቱ የሚከራከርለት አልነበረውም፤ የለውም። ከሠላሳ ዓመት በላይ ማለት ነው። የአርሶ አደሩን ጉዳይ ግብርና ሚኒስቴርና መሰል ተቋማት ናቸው ሲያነሱ የኖሩት፤ መንግሥት ነው ሲያነሳ የኖረው።

የአርሶ አደሮች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከግብዓት አቅርቦት ከምርት ለገበያ በማቅረብ ጋር በተያያዘ ስለ አርሶ አደሩ የሆነ የሆነ ነገር ሲሉ ቆይተዋል። እነሱም በኢሕአዴግ መምጣት ተበትነው ነበርና ይህን ለብዙ ጊዜ ሠርተውታል ሊባሉ አይችሉም። ቆይቶ ቆይቶ ነው እንደገና የተቋቋሙት።

የኢሕአዴግ መንግሥት የደርግ ዘመን ስሪት ያለውን በሙሉ በመዝጋት የሚታወቅ መንግሥት ነበር፤ የኢትዮ ኩባ ወዳጅነት አደባባይ የተባለውን ስፍራ ስንት ዓመት ዘግቶበት እንደነበር የምታስታውሱ ታስታውሳላችሁ። እኔ እስረኛው ሐውልት እለው ነበር። ለመከላከያ ሠራዊት በነበረው ጥላቻ ሐውልቱን ዳዋ እንዲበላው፣ ለድምቀቱ የተሠሩ መብራቶች እንዲወድሙ አድርጓል፤ የቆሻሻ መጣያ ሲሆን ዝም ብሎ ነው የተመለከተው። በኋላ ላይ የኢትዮ ኩባ ወዳጅነት አደባባይ ተባለና ለሕዝብ ክፍት ተደረገ እንጂ ቢያፈርሰው ደስታውን አይችለውም ነበር።

ወደ ጉዳዩ ልመለስ፤ ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው አካላት/መንግሥት ወይም ግብርና ሚኒስቴር፣ የአርሶ አደሮች ኅብረት ሥራ ማኅበራት/ የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በሚያደርጉት ርብርብ አርሶ አደሩን ደግፈውታል። ለምርቱ ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኝ በሚልም ገበያ የመፍጠር ሥራዎችን ሠርተዋል። ከቴክኖሎጂ እንዲተዋወቅ፣ ልምድ እንዲጋራ ሠርተዋል። ለእዚህ ተግባራቸው ባለውለታ ናቸው።

አርሶ አደሩ ማኅበር ቢኖረው ደግሞ በዚህ ላይ ሊጨመረው የሚችለው እንደሚኖር መጠርጠር አይገባም። ችግሮቹን በሙሉ መፍታት ባይችልም፣ የተወሰኑትን መፍታት፣ ማስፈታት ይችላል። ከአንዳንድ ንቁ ማኅበራት መገንዘብ እንደሚቻለው ማኅበር የአባላት መብት ያስጠብቃል፤ የአምራች ድርጅቶች ሠራተኞች ማኅበር ከሆነ ደግሞ መብት ተጠብቆበታል፤ የአምራቾች ማኅበር ከሆነ ደግሞ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ የዘርፉ ደንቃራዎች እንዲወገዱ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይሠራበታል።

በማኅበር መቋቋም ላይ ብዙ አስተያየቶች ይሰነዘራሉ። አንዳንዶች በአንዳንድ ማኅበራት ላይ የታዩ ክፍተቶችን በማሰብ ማኅበር ምን ያደርጋል ሊሉ ይተቻሉ። በገዛ እጅ በላተኛ ማብዛት አርገውም ይቆጥራሉ። አንዳንዶች ደግሞ ቢከፋም ቢለማም ማኅበር እንደሚያስፈልግ ያምናሉ። እነዚህ አካላት ማኅበር እንዲኖር ሲፈልጉ ክፍተቶች እንዳሉ አጥተውት አይደለም።

እርግጥ ነው ሁሉም ማኅበራትን ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ናቸው፤ አባሎቻቸውን ተጠቃሚ ማድረግ ችለዋል ማለት አይቻልም። የማኅበራቱ መሪዎች ከማኅበራቸው ይልቅ ለአሠሪዎች ታማኝ የሆኑበት ሁኔታ ጥቂት አይደለም፤ ይህን ይህን

**በማኅበሩ መዘጋት ሳቢያ ኢሕአዴግ ሀገሪቱን ከተቆጣጠረ አንስቶ አርሶ አደሩ ድምፁን የሚያሰማለት፣ ስለመብቱ የሚከራከርለት አልነበረውም፤ የለውም። ከሠላሳ ዓመት በላይ ማለት ነው። የአርሶ አደሩን ጉዳይ ግብርና ሚኒስቴርና መሰል ተቋማት ናቸው ሲያነሱ የኖሩት**

የተመለከቱ ወገኖች ማኅበርን ቢጠሉ አያስገርምም።

አንዴ አመራሩ ላይ ከወጡ በኋላ የማይወርዱ ጥቂት የማይበሉ የማኅበራት መሪዎች ያሉበት ሁኔታም ሰዎች ማኅበርን እንዲጠራጠሩ ቢያደርግ አያስገርምም። የማኅበራቱ መሪዎች የሥልጣን ቆይታ በጣት ከሚቆጠሩ ዓመታት የማይዘልቅ መሆኑ በሕጋቸውም ሰፍሮ እያለ እነሱ ግን የምንጊዜም፣ የእድሜ ልክ ፕሬዚዳንት፣ ጸሐፊ ወዘተ ሆነው የሚቆዩበት ሁኔታ ጥቂት አይደለም። ከሁለት አስርተ ዓመታት በላይ የማኅበር መሪ የሆኑ አሉ።

እነዚህ መሰል ማኅበራት አሉ ተብሎ ግን ማኅበር ከመመሥረት መቆጠብ አያስፈልግም፤ ለአባሎቻቸው መብት ሲሉ የተሰደዱ፣ በእስር የማቀቁ፣ ተረጋግተው ሥራቸውን እንዳይሠሩ የተደረጉ ጥቂት እንዳልሆኑም ማሰብ ያስፈልጋል። በእነሱ መስዋዕትነት ይነስም ይብዛ የአባላት መብት የተከበረበትን ሁኔታ መዘንጋት አይገባም።

አንዳንዶች ደግሞ ማኅበር ተብዬው ሊያደርግ የሚችለውን አሠሪው ወይም መንግሥት እያደረገ ስለሆነ ማኅበር አያስፈልግም ሊሉ ይችላሉ። መንግሥት ለዘርፉ እድገት ሲል የዘርፉን ተዋናይ ሊደግፍ ይችላል፤ ከእዚያ በዘለለ ግን የማኅበሩን ሚና ሊጫወት አይችልም።

በሀገራችን በርካታ የሙያ ማኅበራት እንዳሉ ይታወቃል። የሠራተኞች ማኅበራትና ኮንፌዴሬሽናቸው፣ የመምህራን ማኅበር፣ የሕክምና ባለሙያዎች ማኅበራት፣ የአሽከርካሪዎች ማኅበር፣ የጋዜጠኞች ማኅበር፣ የወጣቶች ማኅበር፣ የሴቶች ማኅበር.... ተዘርዝረው አያልቁም።

እነዚህ የሙያና የመሳሰሉት ማኅበራት የሠራተኞችን መብቶች ለማስጠበቅ፣ ሙያዊ ነፃነት እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ ከቀጣሪዎች ወይም ከመንግሥት ጋር ሊደረጉ በሚችሉ ውይይቶች ላይ አባላትን በመወከል ይወያዩባቸዋል። በኢንዱስትሪዎች የሠራተኛ ማኅበራት ሚና ጥያቄ የለውም።

ለኢንዱስትሪ ሠላም መጠበቅ፣ ለምርትና ምርታማነት የበለጠ ማደግ የሠራተኛው ሚና ወሳኝ እንደመሆኑ ማኅበራቱም የበኩላቸውን ያደርጋሉ። ማኅበራት ለአባሎቻቸው እንደ ሥልጠና፣ የአቅም ግንባታ ድጋፎችን የመሳሰሉትን የሚያደርጉበት ሁኔታም ይታያል።

በሠራተኛውና በአሠሪው መካከል የሚደረጉ ውይይቶች በሠለጠነ አግባብ እንዲፈጸሙ የሠራተኛ ማኅበር ወሳኝ ሚና ይጫወታል። የሁሉም ድምር ውጤት ሠራተኛው መብቱ ተጠብቆ ኃላፊነቱን በሚገባ እንዲወጣ እንዲሁም ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ማድረግም ነው።

የሠራተኛው መብት ተጠበቀ ማለት፣ ሠራተኛው በነፃነት የሚሠራበት ሁኔታ ተፈጠረ ማለት ሥልጠናና የመሳሰሉትን በማኅበሩ በኩል አገኘ ማለት ምርታማነቱ ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያርፋል ማለት ነው።

ወደ አርሶ አደሩ ማኅበር እንምጣ። ኢትዮጵያ የአርሶ አደሮች ሀገር ናት፤ የቅርብ ጊዜ መረጃ ባይኖርም ከሀገሪቱ ሕዝብ 85 በመቶው አርሶ አደር ነው ይባላል። ይህን አኃዝ ኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፉ እየቀነሰው ሊመጣ ቢችልም፣ አኃዙ ብዙም የሚነቃነቅ አይሆንም።

አርሶ አደሩን ያቀፈው የግብርናው ዘርፍ ከሀገሪቱ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ከፍተኛውን እጅ የሚይዝ ነው፤ በአገልግሎቱና ኢንዱስትሪው ላይ በተከናወነ ተግባር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እነዚህ ዘርፎች በአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ እየጨመረ ቢመጣም ግብርናው ከፍተኛውን ድርሻ እንደያዘ ነው ።

የዚህ ምጣኔ ሀብት ዋና ተዋናይ አርሶ አደር የእኔ የሚለው ማኅበር ቢኖረው ዘርፉ ይበልጥ ያድጋል፤ ከሌሎች ዘርፎች ጋር የሚኖረው ትስስርም የበለጠ ይጠናከራል እንጂ አይጎዳም። መንግሥት እንደ መንግሥት የሚያደርገው ድጋፍ እንዳለ ሆኖ አርሶ አደሩ በማኅበር ተደራጅቶ በመንቀሳቀሱ በግብርናው ላይ የሚያመጣው ለውጥ ሊኖር እንደሚችል ጥርጥር የለውም።

ይህን አጋርነት ፈጥኖ ማምጣት ግብርና የበለጠ እንዲመነደግ ማድረግ ሊሆን ይችላል። የማኅበር ጥያቄው ፈጥኖ እንዲመለስ ማድረግ ይገባል፤ ይህን ማጓተት መጅ እንደመደበቅ ይቆጠራል። ይህን ዘርፍ የሚያንቀሳቅሰው አርሶ አደር ከሦስት አስርተ ዓመታት በፊት አረረም መረረ ስለራሱ የሚናገርበት የራሱ የሆነ መድረክ ነበረው። የመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበር የተሰኘ። ከላይ ጠቅሼዋለሁ።

ኢሕአዴግ ሀገሪቱን ሲቆጣጠር ይህ ማኅበር ሕልውናውን እንዲያጣ አደረገው እንጂ ትልቅ ማኅበር ነበር። «ረጅም ጦር ባይወጉበት ያስፈ ራሩበት» እንደሚባለው ማኅበር መመሥረት ፋይዳ አለው። መኖሩ የአርሶ አደሩን መብት ለመግፈፍ የሚንቀሳቀሱ ካሉ እንዲታቀቡ ማድረግ ያስችላል። በማዳበሪያ በምርጥ ዘር በቴክኖሎጂ አቅርቦት በኩል ያሉትን ጥያቄዎች ሊያነሳበት ይችላል። አህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ አጋርነት ቢመሰረትበትስ።

እኔ በዚህ ጉዳይ ላይ የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም ከሚሉት አይደለሁም። በሌሎች ማኅበራት ላይ የሚታየው ጉድለት አዲስ በሚቋቋም ማኅበር ላይ ሊከሰት ይችላል ብዬ ማኅበሩ አለመቋቋሙን አልደግፍም። የሆነ ችግር ሊፈታ ይችላል የሚል እምነት አለኝ።

ይህን መሥራት ማለት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ መሥራት ነው፤ አርሶ አደሩ ለምርቱ ተገቢውን ገበያ እንዲያገኝ መሥራት ነው። የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማሳደግ መሥራት ነው። አርሶ አደሩ በማኅበር ተደራጅቶ መብቱን እንዲያስከብር አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር ነው ።

በራሱ ብርቱዎችን ለመሸለም፣ ደካሞችን ለማጠንከር የሚችልበት እድል እንዲኖረው ማስቻል ነው። የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮ መጋራት፣ ከአቻ ማኅበራት ጋር በመሥራት የግብርናውን ዘርፍ ይበልጥ ማሳደግ፣ ሕይወቱን ወደ ተሻለ ደረጃ ማሸጋገር የሚያስችለውን ሁኔታ መፍጠር ነው ።

"ረጅም ጦር ባይወጉበት ያስፈራሩት" እንደሚባለው የማኅበሩ መኖር አፍጠው፤ አግጠው ሊመጡ የሚችሉ ችግሮችን በጋራ ለመቋቋም ይጠቅማል። የማኅበሩ መኖር በራሱ አንዳንድ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ያስችላል። አርሶ አደሩ ማኅበሩን በመመሥረቱ ብቻ ሊፈጠር የሚችል ሥነ ልቦናዊ ተፅዕኖ /ተጠቃሚ የሚያደርገው ሊኖር እንደሚችል ማሰብ ተገቢ ይመስለኛል። የማኅበሩ መኖር በራሱ ትልቅ ፋይዳ አለውና ማኅበሩን እውን ለማድረግ ሀሳቡን ያነሳችሁ ጥረታችሁን አጠናክራችሁ ቀጥሉ።

ለአርሶ አደሩ የቅርብ ድጋፍ የሚያደርጉ መንግሥታዊ አካላት፣ ሌሎች የዘርፉ አካላት ለእዚህ ማኅበር እውነትነት ሊተጉ ይገባል። የአርሶ አደሮች ቀን እንዲከበር የአርሶ አደር ማኅበር እንዲመሠረት ሀሳቡን ያነሳችሁ ያዳበራችሁ በቀጣይም በዚህ ላይ ለመሥራት ኃላፊነቱን የወሰዳችሁ ሁሉ ምስጋና ይገባችኋል። እደገመዋለሁ፤ ማኅበሩ እውን እንዲሆን ሀሳቡን ያነሳችሁ አካላት ርብርባችሁን አጠናክራችሁ በመቀጠል ታሪክ ሥሩ እላለሁ።

# የጨው አምራችና አቀነባባሪ ፋብሪካዎች ፈተና- የዋጋ ተመን ዝቅተኛነት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

መንግሥት የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ችግሮች ለማቃለል የተለያዩ ተግባሮች እያከናወነ ይገኛል። ከእነዚህም መካከል የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ይጠቀሳል። በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ አቁመው ከነበሩ ኢንዱስትሪዎች መካከል በርካታ የሚባሉት በንቅናቄው ወደ ሥራ ተመልሰዋል። ንቅናቄው በሀገር አቀፍ ደረጃ ለአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ እድገት ተስፋ ሰጪ የሆኑ ውጤቶች እንደተመዘገቡበት በተለያዩ መድረኮች ተጠቁሟል።

በሀገሪቱ አምራቾችና ተጠቃሚዎች የሚያስተሳስሩ፣ ግብዓት አቅራቢዎችንና አምራቾችን የሚያቀራርቡ ባዛርና ኢግዚቢሽኖችም በተለያዩ አካላት እየተካሄዱ ይገኛሉ። ጎን ለጎን የሚካሄዱ ውይይቶችም የዘርፉን መልካም አጋጣሚዎች ለመጋራት ችግሮችን ለማዳመጥና መፍትሄ ለማመላከት እያገለገሉ ናቸው።

እንደ ሀገር ተጠናክሮ በቀጠለው በዚህ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢንዱስትሪዎችና ኢንተርፕራይዞች ወደ ሥራ ስለመግባታቸው የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዞች ልማት መረጃ ያመላክታል። ከሰሞኑም የዚህ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ አንድ አካል የሆነው ባዛርና ኤግዚቢሽን በአዲስ አበባ ስካይላይት ሆቴል ተካሂዷል።

‹‹ኢትዮጵያ ታምርት እኛም እንሸምት›› በሚል መሪ ሃሳብ በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አዘጋጅነት የተካሄደው ይህ ባዛርና ኤግዚቢሽን የሀገር ውስጥ ምርቶችን በማስተዋወቅና የገበያ ትስስር በመፍጠር ትልቅ ድርሻ እንደነበረው ተሳታፊዎች አረጋግጠዋል። በተለይም ተኪ ምርቶችን በማበረታታት ለሀገራዊ ኢኮኖሚ እድገት እያበረከተ ያለው ድርሻ ጉልህ መሆኑ ተጠቁሟል።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዞች ልማት መረጃ እንዳመላከተው፤ ለአምስት ቀናት በተካሄደው በእዚህ ኤግዜቢሽንና ባዛር 85 የሚደርሱ ኢንዱስትሪዎችና ኢንተርፕራይዞች ተሳትፈዋል። ከእነዚህም መካከል የአልባሳት፣ ቆዳና የቆዳ የውጤቶች፣ የእጅ ሥራዎች፣ የኢንዱስትሪ ውጤቶች እንዲሁም ምግብና ምግብ ነክ የሆኑ ምርቶችን ይዘው የቀረቡት ይጠቀሳሉ።

የምግብ ጨው አምራችና አቀነባባሪዎችም በኢግዚቢሽንና ባዛሩ ተገኝተዋል። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ሰዎች በአዮዲንና ተያያዥ የምግብ ንጥረ ነገር እጥረት ምክንያት ለተለያዩ በሽታዎች ይጋለጣሉ። በአዮዲን እጥረት ከሚከሰቱ የጤና እክሎች መካከል የአዕምሮ ውስንነት፣ ጎይተር (እንቅርት)ና የመቀንጨር ይጠቀሳሉ። እነዚህን የጤና እክሎች ለመከላከልም የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ይስተዋላል። መንግሥት በአዮዲን የበለጸገ ጨው ለማህበረሰቡ በስፋት ለማቅረብና ተደራሽነቱን ለማሳደግ ጥረቶችን ያደርጋል።

ኢትዮጵያ በአዮዲንና ተያያዥ የምግብ ንጥረ ነገር እጥረት ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማከም በየዓመቱ ከ55 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ መረጃዎች ይጠቁማሉ። መንግሥት በሀገሪቱ የሚገኘውም የጨው ሀብት በአዮዲን በማበልፀግ የሀገር ውስጥ ፍጆታን ከመሸፈን ባለፈ ለኢንዱስትሪ ግብዓት ለማቅረብ፣ የጨው ምርት ዓለም አቀፍ ደረጃውንና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ እንዲመረት ለማድረግ የሚካሄዱ ተግባሮችን ይደግፋል።

ይህ ሁሉ ተሠርቶም የገበያ ሁኔታውን ጨምሮ በጨው ማምረትና ግብይት ወቅት የተለያዩ ችግሮች እንደሚከሰቱ ይጠቆማል። ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት እኛም እንሸምት›› በሚል መሪ ሃሳብ በተካሄደው በዚህ ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ የተሳተፉ ጨው አምራችና አቀነባባሪዎችም ይህንኑ አረጋግጠውልናል። በተለይ መንግሥት ለፋብሪካዎች ያስቀመጠው የጨው መሸጫ ዋጋ በሥራቸው ላይ እንቅፋት እየፈጠረባቸው መሆኑን ነው እነዚህ አካላት ያመለከቱት።

በባዛርና ኤግዚቢሽኑ ከተሳተፉት የምግብ ጨው አምራችና አቀነባባሪዎች መካከል አሽ አሌ ጨው ማምረቻና ማቀነባበሪያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር /ፋብሪካ/ አንዱ ነው። ፋብሪካው በአፋር ክልል በርሃሌ ወረዳ ዞን ሁለት አካባቢ ነው የሚገኘው። ፋብሪካው የተለያዩ ችግሮችን በመቋቋም ጥሬ ጨው ከአምራቾች እየተረከበ ሙሉ ለሙሉ አዮዳይዝድ በማድረግ ለገበያ ያቀርባል።

የፋብሪካው የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ጥላዬ ይትባረክ እንዳሉት፤ ተፈላጊ ግብዓቶችን አሟልቶ ደረጃውን በጠበቀ መንገድ የምግብ ጨው እያመረተ ለገበያ የሚያቀርበው አሽ አሌ የምግብ ጨው ፋብሪካ በ33 ሺ ካሬ ሜትር ስፋት ባለው ቦታ ላይ ያረፈ ነው። ፋብሪካው በተወሰኑ ባለድርሻ አካላት በ400 ሚሊዮን ብር የተከፈለ መነሻ ካፒታል የተቋቋመ ሲሆን፣ በሰዓት 40 ቶን የምግብ ጨው የማምረት አቅምም አለው።

‹‹በኢትዮጵያ ታምርት እኛም እንሸምት›› በሚል መሪ ሃሳብ በተዘጋጀው ባዛርና ኤግዚቢሽን በመሳተፍ ምርትና አገልግሎታቸውን ከማስተዋወቅ ባለፈ በዘርፉ እያጋጠመው ያለውን ችግርም ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ መቻሉን አቶ ጥላዬ ይገልጻሉ። ባዛርና ኤግዚቢሽኑ የገበያ ትስስር በመፍጠር፣ ከግብዓት አቅራቢዎች ጋር ለመገናኘትና ምርትና አገልግሎታቸውን ለማስተዋወቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ ማበርከቱንም ጠቁመዋል።

ከዚህ ቀደም የምግብ ጨው ያመርት የነበረው በባህላዊ መንገድ በመንፌያ በመጠቀም በሰው ጉልበት መሆኑን አስታውሰው፣ በአሁኑ ወቅት ግን ከፍተኛ ወጪ በማድረግ ዘመናዊ በሆኑ ማሽነሪዎች በመጠቀም እያመረተ ይገኛል ብለዋል። ፋብሪካው የሚያመርተው የምግብ ጨው ሙሉ ለሙሉ አዮዳይዝድ የሆነና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑንም አስታውቀዋል።

የምግብ ጨው ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለ የጠቀሱት አቶ ጥላዬ፤ የገበያ ችግር እንደሌለም አስታውቀዋል። ፋብሪካው ችግር የሆነበት በሚያመርተው የምግብ ጨው ላይ በመንግሥት የተጣለው የመሸጫ ዋጋ ተመን ዝቅተኛነት ላይ መሆኑን ጠቁመዋል።

ፋብሪካው ጥሬ ጨው ከአምራቾች ተረክቦ አቀነባብሮና አስፈላጊውን ሂደት አልፎ ለምግብነት እንዲውል ለማድረግ ከፍተኛ ወጪ እንደሚያደርግ አቶ ጥላዬ ተናግረዋል። ይህ ወጪ መንግሥት ከጣለው የመሸጫ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም በሥራው ላይ እንቅፋት ፈጥሮበታል ብለዋል። መንግሥት አንድ ኩንታል ጨው ከፋብሪካ እንዲወጣ በተመነው ዋጋ መሠረት ጨው እያመረተ ለገበያ የሚያቀርበው አሽ አሌ፣ ጨው ማምረቻና ማቀነባባሪያ ፋብሪካ ምርቱን በኪሳራ እየሸጠ መሆኑንም ነው ያመለከቱት።

በአካባቢው በተካሄደው ጦርነት የተነሳ ፋብሪካው ለዘረፋና ውድመት መዳረጉንም አስታውሰው፣ ፋብሪካው ግን እነዚህን ችግሮች ሁሉ ተቋቁሞ በአሁኑ ወቅት በሁለት እግሩ በመቆም በሙሉ አቅሙ እያመረተ መሆኑን አስታውቀዋል። በጦርነት ወቅት ለደረሰበት መጠነኛ ጉዳትና ዘረፋም የክልሉን መንግሥት ጨምሮ የፌዴራል መንግሥት ድጋፍ ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

አቶ ጥላዬ እንዳመለከቱት፤ ፋብሪካው ከመንግሥት ያገኛቸውን የተለያዩ ድጋፎች ምርኩዝ አድርጎ ያለምንም የባንክ ብድር ተቋቁሞ ወደ ሥራ የገባ ቢሆንም፣ በአሁኑ ወቅት ግን መንግሥት በጣለው የጨው መሸጫ ዋጋ ተጎጂ እየሆነ ነው። ፋብሪካው በምግብ ጨው ውስጥ አስፈላጊዎቹን ንጥረ ነገሮች ከማሟላት በተጨማሪ ለጨው ምርት ማሸጊያ የሚውሉ ማሸጊያዎችን ከፋብሪካዎች ገዝቶ ይጠቀማል፤ ይህም ሌላው ወጪው ነው። ለሰው ኃይል የሚደረገው ክፍያና የነዳጅ ዋጋም በየጊዜው እየጨመረ ነው።

ይህ የማምረቻ ወጪና መንግሥት ያወጣው የአንድ ኩንታል ጨው መሸጫ ዋጋ አይጣጣምም ሲሉ አመልክተው፣ ይህም በፋብሪካው ሥራ ላይ ችግር መፍጠሩን አስታውቀዋል። መንግሥት ችግሩን ተረድቶ በዋጋው ላይ በድጋሚ ክለሳ እንዲያደርግ አቶ ጥላዬ ጠይቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ እሳቸው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በጨው ዋጋ ላይ የሚጣለው ዋጋ እና ለማምረት የሚወጣው ወጪ ከፍተኛነት አሳሳቢ ስለመሆኑ ለመንግሥት እያስረዱ ናቸው፤ ችግሩ የትኛውንም ያህል ፋብሪካውን እየፈተነ ቢሆንም፣ ፋብሪካው ከማምረት ሥራው ግን አልተቆጠበም። ሥራውን እየሠራ ጥያቄውን ማቅረቡን ቀጥሏል።

> **መንግሥት አዮዳይዝድ የሆነ ጨው ለማህበረሰቡ ለማቅረብ የሚያደርገውን ጥረት በብርቱ ከሚደግፉ ጨው አምራቾችና አቀነባባሪዎች ጋር በቅርበት መሥራት ይኖርበታል። ለእዚህም ጨው አምራቾችና አቀነባባሪዎች ጨው ለማምረት የሚያወጡትን ወጪ አጥንቶና አስልቶ የዋጋ ተመኑንም ሊያስተካክል ይገባል**

መንግሥት አዮዳይዝድ የሆነ ጨው ለማህበረሰቡ ለማቅረብ የሚያደርገውን ጥረት በብርቱ ከሚደግፉ ጨው አምራቾችና አቀነባባሪዎች ጋር በቅርበት መሥራት እንዳለበት ያመለከቱት አቶ ጥላዬ፤ ጨው አምራቾችና አቀነባባሪዎች ጨው ለማምረት የሚያወጡትን ወጪ አጥንቶና አስልቶ የዋጋ ተመኑን ሊያስተካክል እንደሚገባ አመልክተዋል፤ አዮዳይዝድ የሆነና ለጤና ተስማሚ የሆነ የምግብ ጨው አሁንም ድረስ ገበያው ላይ በበቂ ሁኔታ ተደራሽ እንዳልሆነ ገልጸው፤ ለዘርፉ ትኩረት ቢሰጥ መልካም ነው ብለዋል።

ከአፍዴራ ሀይቅ የሚወጣውን ጨው ለአቀነባባሪዎች የሚያስረክበው አፍዴራ ጨው አምራቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ ህብረት ሥራ ማህበር ሌላኛው የዘርፉ ተዋናይ ነው። ማህበሩ ሁለት ሺ 650 የሚደርሱ አባላት አሉት። ጥሬ ጨው በአግባቡ ከአምራቾች በመሰብሰብ ለፋብሪካዎች ያስረክባል።

የአፍዴራ ጨው አምራቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ የህብረት ሥራ ማህበር የግብይት ዘርፍ ኃላፊ ወይዘሮ ጽጌ በለጠ ፋብሪካዎች ከአምራቹ የተሰበሰበውን ጨው አስፈላጊውን እሴት ጨምረው ለምግብነትና ለኢንዱስትሪ እንደሚያቀርቡ ይገልጻሉ። ጥሬ ጨውን አጥበው አድርቀውና እሴት ጨምረው እንዲሁም ለምግብነት የሚውለውን ደግሞ አዮዳይዝድ በማድረግ ለገበያ እንደሚያቀርቡ ጠቅሰው፣ ለፋብሪካ የሚውለውንም እንዲሁ እንደ ደንበኞቹ ፍላጎት የሚታጠብ ከሆነ አጥበው፤ የማይታጠብ ከሆነም ሳይታጠብ ያቀርባሉ ይላሉ። ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት የሚውለው ጨው ናፍታሊም የተባለ ጋዝ ተረጭቶ ለገበያ እንደሚቀርብ ጠቅሰው፣ ይህም አዮዳይዝድ ያልሆነ ጨው ለምግብነት እንዳይውል የመከላከያ አንዱ መንገድ ነው ብለዋል።

ሰዎች አዮዳይዝድ የሆነና አስፈላጊውን ንጥረ ነገር ያሟላ ጨው መመገብ እንዳለባቸው የጠቀሱት ወይዘሮ ጽጌ፤ አዮዳይዝድ ያልሆነ ጨው መመገብ የጤና ችግሮችን የሚያስከትልና በተመሳሳይ ደግሞ ከጨው የሚገኘውን ጥቅም የሚያሳጣ መሆኑን ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ጨው በሁለት መንገድ ተዘጋጅቶ ለገበያ ይቀርባል። አርሶ አደሩ የተለያዩ ሂደቶችን አልፎ የሚያወጣውን የጥሬ ጨው ምርት ማህበሩ ሰብስቦ ለፋብሪካዎች ያቀርባል። በሄክታር በሄክታር ተከፋፍሎ የሚገኘውን የጨው ክምር ህብረት ሥራ ማህበራቱ በምድብ ቦታቸው ተገኝተው አርሶ አደሩ ቆፍሮና በብዙ ድካም ያወጣውን የጨው ክምር በማዳበሪያ እያዘጋጁ ወደ ፋብሪካዎች ያደርሳሉ። አንድ ማዳበሪያ ጨው ከ50 እስከ 52 ኪሎ ግራም የሚይዝ ቢሆንም፤ ለሽያጭ ወደ ፋብሪካዎቹ ሲቀርብ በኩንታል ነው። አንድ መኪና አራት መቶ ሃያ ኩንታል ይይዛል። ማህበሩ በዚህ መሰረት ያዘጋጀውን ጥሬ ጨው ለፋብሪካዎች ያቀርባል።

በአንድ ወር ውስጥ ለሀገሪቷ የሚያስፈልገው የጨው መጠን ምን ያህል እንደሆነ በመንግሥት እንደሚወሰን ወይዘሮ ጽጌ ጠቅሰው፤ ከምርት መጠኑ በተጨማሪም የመሸጫ ዋጋውም በመንግሥት እንደሚወሰን ተናግረዋል። በሀገሪቱ የሚገኙት ጨው አምራችና አቀነባባሪ ፋብሪካዎች ከህብረት ሥራ ማህበራቱ ጋር በሚገቡት ውል መሠረት ጥሬ ጨው ተረክበው እሴት በመጨመር ለገበያ ያቀርባሉ ብለዋል።

ጨው አቀነባባሪ ፋብሪካዎች ከመንግሥት በሚያገኙት ፈቃድ መሠረት ወደ ምርት ሲገቡ ከጨው አምራችና አቅራቢዎች ጋርም እንዲሁ ውል በማሰር ነው ያሉት ወይዘሮ ጽጌ፤ መንግሥት ያስቀመጠውን የወር ፍጆታ መጠን መሠረት በማድረግ ከጨው አምራችና አቅራቢዎች ጋር ውል እንደሚገባም አስታውቀዋል። በገቡት ውል መሠረትም በወር ውስጥ ምን ያህል የጨው ምርት ከአምራችና አቅራቢው እንደሚያገኙ እንደሚታወቅ ጠቅሰው፣ ማህበራቱ ከመንግሥት በሚያገኙት ፈቃድ መሠረት በጠቅላላው እስከ 650 ሺ ኩንታል ጨው ለፋብሪካዎች ይቀርባሉ ብለዋል።

ወይዘሮ ጽጌ እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ በስፋት የሚሰራጨው የአፍዴራ ጨው ነው። ማህበራቱ መንግሥት ባስቀመጠላቸው ኮታ መሠረት ምርቱን በየወሩ ለፋብሪካዎች ያቀርባሉ። በወር ውስጥ ከሚያስፈልገው የጨው መጠን በላይ አይመረትም፤ አልፎ አልፎም በተለይ በክረምት ወቅት የጨው ምርት ተፈላጊነት የሚቀንስበት ወቅትም አለ።

እሳቸውም የጨው መሸጫ ዋጋው በመንግሥት እንደሚተመን ጠቅሰው፣ የዋጋ ተመኑ አምራቹን እየጎዳው መሆኑንም አስታውቀዋል። መንግሥት የዋጋ ተመኑን በተለያየ ጊዜ እንደሚያሻሽል ጠቅሰው፣ አርሶ አደሩ በጨው ምርት ሂደት ውስጥ ከሚጠበቅበት ድካም አንጻር ዋጋው ግን ተመጣጣኝ አይደለም ብለዋል።

ለአብነትም በቅርቡ የጨው መሸጫ ዋጋ ከመሻሻሉ በፊት አንድ ኩንታል ጨው 283 ብር ከ57 ሳንቲም እንደነበር ጠቅሰው፣ ይህ ማለት አንድ ኪሎ ጨው በአማካኝ ሁለት ብር ከሰማንያ ሳንቲም አካባቢ ይሸጥ እንደነበር አስታውሰዋል፤ በቅርቡ መንግሥት ባደረገው ማሻሻያ መሠረት አንድ ኩንታል ጨው 557 ብር ከ88 ሳንቲም እንዲሸጥ መወሰኑን አስታውቀዋል። ይህም ቢሆን አርሶ አደሩ ጨው ለማምረት ከሚያወጣው ወጪና ድካም አንጻር አሁንም ተመጣጣኝ ዋጋ አለመሆኑን አስገንዝበዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የኩረጃ ነገር አይመረመርም!

**ዋስልኝ አየለ**

‹‹የሥጦታ ፈረስ ጥርሱ አይታይም›› እንደሚባለው ነው መሰለኝ የኩረጃ ነገር አይጠየቅም፤ አይመረመርም። የፈተና ኩረጃ የሰነፍ ተማሪ ምልክት ነው። የባህል ኩረጃ ደግሞ የሰነፍ ሕዝብ ምልክት መሆኑ ነው። ሰነፍ ተማሪ ሲኮርጅ ለመኮረጅ ቀላል የሆኑ ነገሮችን ነው የሚኮርጅ። ምርጫ፣ እውነት ሐሰት፣ አዛምድ እና ባዶ ቦታ ሙላ የመሳሰሉትን፤ በቀላሉ አይቶ የሚጻፉትን ማለት ነው። ቀመራዊ አሠራር ወይም ሌላ ሰፊ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸውን አይኮርጅም። አንደኛው ምክንያት ሲኮርጅ ፈታኙ መምህር ይደርስበታል። ሁለተኛው ምክንያት ግን ቢፈቀድለት ራሱ አይችልም። ያንን ውስብስብ ቀመራዊ አሠራር አይችለውም። ተለዋዋጭን በተለዋዋጭ ተክቶ፣ ቅንፍ የሚከፈትበትን ከፍቶ የሚዘጋበትን ዘግቶ፣ የሚጣፋውን አጣፍቶ ቀመሩን በትክክል ሊያስቀምጠው አይችልም። ማድረግ የሚችለው የምርጫና የእውነት ሐሰት መልሶችን ብቻ መኮረጅ ነው።

የፈረንጅ ባህል የመኮረጅ ልማዳችንም እንደዚሁ ሰነፍ ተማሪ ነው። የምንኮርጀው ቀላል ቀላሉን ነው። ለምሳሌ የተራቆተ አለባበስ ስንኮርጅ የልብስ አሠራሩን ግን አንኮርጅም። ምክንያቱም ከእንብርት በላይ የሆነ ልብስ መልበስ በጣም ቀላል ነው፤ ምንም እውቀትና ጥበብ አይጠይቅም። ያንን ልብስ መሥራት ግን እውቀትና ብቃት ይጠይቃል። የፈረንጆችን ይቅርና የራሳችንን የልብስ አሠራር እንኳን አንችልም። እናቶቻችን የዛፍ ፍሬ (ጥጥ) ለቅመው ልብስ እስከሚሆን ድረስ የሚሄዱትን የአሠራር ቅደም ተከተል እንኳን አናውቀውም። ልብስ ከጥጥ እንደሚሠራ እንጂ እንዴት እንደሚሠራ አናውቅም። ይሄን እናቶቻችን የሚያደርጉትን ነገር ያልቻልን ግን የፈረንጅ አለባበስ እንኮርጃለን።

በነገራችን ላይ ኩረጃ ጥበብም ነው። የሰው ልጅ ሲወለድ ከየትኛውም ሙያ ጋር አይወለድም። በማህበራዊ ሕይወቱ ውስጥ ነው የሙያና የተሰጥኦ ባለቤት የሚሆነው። አንዳንድ ሙያዎች ልዩ ተሰጥኦ ቢፈልጉም አብዛኛው ግን በልምድ የሚመጣ ነው። በልምድ ውስጥ ማለት እንግዲህ አንዱ ሌላውን እያየ ማለት ነው። ይሄ ማለት በቀጥታ ኩረጃ ማለት ነው። ልዩነቱ የኩረጃው አይነት ነው። ጎበዝ ማለት ቀጥታ መገልበጥ ሳይሆን ካየው ነገር ተነስቶ ለራሱ በሚስማማ መንገድ መሥራት ማለት ነው። ችግሩ እኛ የምንኮርጀው የሰነፍ ኩረጃ ነው። ይሄ ደግሞ ሁሌም ጥገኛ ያደርጋል።

የባህል ኩረጃና የባህል ወረራ ከሚነሳባቸው ነገሮች አንዱ አሁን ያለንበት የገና ሰሞን ነው። በየሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች የገና በዓል ማስታወቂያዎች ተጀምረዋል። በየዓመቱ በዚህ ሰሞን በየሆቴሎች በር ላይ የምናየው አንድ የተከናነበ አርቲፊሻል ሽማግሌ ነው። ይህ ሽማግሌ የፈረንጆች የገና አባት ነው። እውነት እኛ ለዚህ የሚበቁ የጥንት አባቶች የሉንም? የገና ዛፍ ተብሎ በውድ ዋጋ የሚሸጥ አርቲፊሻል ዛፍ በትልልቅ የገበያ ቦታዎች ይታያል። እውነት እኛ ሀገራዊ የገና መጫወቻ አልነበረንም? ከተሞች ውስጥ ግን ይሄ ባህላዊ ገና አይታይም።

ይህ የሶስት ማዕዘን ቅርፅ ያለው የፈረንጆች አረንጓዴ ዛፍ፤ በጥንት ጊዜ ጀርመናውያን ያመልኩበት እንደነበረ እና፤ ቅዱስ ቢኒፋሴ የተባሉ ቄስ ነገሩን ለማስቀረት በሥላሴ ተምሳሌነት ይጠቀሙበት እንደነበረ፤ መረጃዎች ያሳያሉ። በኋላም በተለያዩ ጌጣጌጦች እያሸበረቀ መጣ። እኛ ኢትዮጵያውያን ይሄን ኮርጀን ስንገለብጥ ግን ምን እንደሆነ እንኳን ሳናውቅ ነው። ባህላዊም ይሁን ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን የራሳችን የሆኑ ነገሮችን በመጣል ነው። ፈረንጆች የገና አባት የሚሉት ‹‹ሳንታ ክላውስ›› ምናባዊ ይሁን እውነተኛ አከራካሪ በሆነበት፤ በሀገራችን የታወቁ ሰዎችን ግን የእርሱን ያህል ክብር አያገኙም።

ይህ ማለት ግን በሁሉም ቦታዎች ነው ማለት አይደለም። ከሁለት ይሁን ሦስት ዓመት በፊት ያየሁት ነበር። አንድ የምግብ ቤት በር ላይ (ጉርድ ሾላ አካባቢ) በትልቁ የተጻፈ የተዘጋጀ ሸራ ላይ፤ እንደ መሰንቆ፣ ክራር፣ ከበሮ፣ በገና የመሳሰሉ የባህል የሙዚቃ መሣሪያዎች ተደርድረዋል። ከመሃል ላይ ደግሞ ባህላዊ ገና በትልቁ ይታያል። እንዲህ አይነት በባህሉ የሚኮራ ሰውም አለ ማለት ነው። ልብ በሉ! ቤቱ የሙዚቃ መሣሪያ ወይም ገና የሚሸጥበት ሳይሆን ምግብ ቤት ነው። ያንን ቤት ያየ ፈረንጅ ሁሉ ኢትዮጵያን አወቀ ማለት ነው። የገና አባት ቢሆን ግን ምንም የተለየ ስሜት አይፈጥርበትም።

በነገራችን ላይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለውጥ እየመጣ ይመስላል። አስታውሳለሁ 2005፣ 2006 እና 2007 ዓ.ም አካባቢ በየመገናኛ ብዙኃኑ ይቀርብ የነበረ ወቀሳ ‹‹የራሳችን ነገር ተረሳ›› የሚል ነበር። የፈረንጅ አምላኪዎች መሆናችን በየጋዜጦችና መጽሔቶች ወቀሳ በዝቶበት ነበር። ምናልባት ያ የመጣው ለውጥ ይሁን በሌላ ምክንያት ባይታወቅም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የቴሌቭዥን ጣቢያዎች ባህላዊውን የገና ጨዋታን ማሳየት ጀምረዋል። ማስታወቂያዎች በባህላዊ የገና ጨዋታ መታጀብ ጀምረዋል። ቢያንስ በመገናኛ ብዙኃን ደረጃ ይህን ያህል ለውጥ መታየቱ ይበል ያሰኛል።

በዚያው ልክ ግን ለባህል ወረራው ምክንያቶችም መገናኛ ብዙኃን ናቸው። መገናኛ ብዙኃኑ ጎንደር ላይ ያለ፣ አክሱም ላይ ያለ ወይም ቦረና ላይ ያለ የገና በዓል አከባበርን ከሚያቀርብ ይልቅ ፈረንሳይ ወይም ጃፓን ወይም ዱባይ ውስጥ ያለውን እየደጋገመ ስለሚያሳይ ተፅዕኖ መፍጠሩ የግድ ነው። መገናኛ ብዙኃን ከፍተኛ ኃይል አላቸው። ለብዙ ዘመናት የኖረውን ባህል ነው አሥር እና አሥራ አምስት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የባህል ወረራውን ያፋጠኑት። የሚሠሩትም ገንዘብ ያለበት ቦታ ላይ ስለሆነ ነው ስለሀገራዊ ገጽታው የማይጨነቁት። ገበያው በሞቀበት አካባቢ ከማስታወቂያ ሥራዎች ጀምሮ ይረባረቡበታል።

ይሄ ሁሉ ሲሆን ግን ማህበረሰቡ ላይም ችግር የለም ማለት አይደለም። የፈረንጅ ባህል መከተል መሰልጠን የሚመስለው ሰው ብዙ ነው። ከፈረንጆች፤ የፈጠራ ሥራዎቻቸውን፣ የንባብ ባህላቸውን፣ ሰዓት የማክበር ልምዳቸውን... አንኮርጅም። የምንኮርጀው በቀላሉ መተግበር የምንችለውን ነገር ነው። ልጆችም የሚያድጉት ይህን እያዩ ነው። ከጥጥ ልብስ መሥራት እንደሚቻል ለልጇ የምታሳይ እናት የለችም። ስለገና አባት ልጁን የሚያስተምር አባት ስለኢትዮጵያዊው የገና ጨዋታ ግን አይነግረውም። አርቲፊሻል ሽጉጥ ለልጁ የሚገዛ አባት ስለሞፈርና ቀንበር ግን አይነግረውም። ልጁ ሲያድግ ገበሬ ይሆናል ባይባል እንኳን የአባቶቹን ጥበብ ማወቅ ነበረበት።

የኩረጃ ነገር እንደዚህ ነው፤ ከሁለቱም ያሳጣል። የራስን እንዳያውቁ ያደርጋል የሰዎችንም በትክክል እንዳይተገብሩ ያደርጋል። የፈረንጆች የሸቀጥ ማራገፊያ ስንሆን የራሳችንን ግን ማንም ፈረንጅ እንዳይገዛው እያደረግን ነው። እንኳን ፈረንጅ ራሳችንም ንቀነዋል። የቱንም ያህል ጥንካሬ ይኑረው ከኢትዮጵያዊ ዕቃ ይልቅ የፈረንጅ ዕቃ የሥልጣኔ ምልክት ይመስለናል። የቱንም ያህል ጤናማ የምግብ ይዘት ይኑረው ከኢትዮጵያዊ ባህላዊ ምግብ ይልቅ በፈረጅ አዘገጃጀት የተዘጋጀው የሥልጣኔ ምልክት ይመስለናል።

የውጭውን ማወቅ ዘመኑ የሚያስገድደው ዓለማቀፋዊነት ነው፤ ዳሩ ግን የራስን እየረሱና እያጣጣሉ መሆን የለበትም!

# ዓለም አቀፍ




## በሕገ-ወጥ መንገድ ሰው ሲያዘዋውር ነበር ተብሎ የታገተው አውሮፕላን ሕንድ አረፈ

በርካታ ሕንዳውያንን ያሳፍረውና ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ሰዎችን እያዘዋወረ ነው ተብሎ የተጠረጠረው አውሮፕላን በስተመጨረሻ ሕንድ አርፏል። አውሮፕላኑ ፈረንሳይ የሚገኝ አውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ለቀናት እንዲቆይ ተደርጓል።

ኤርባስ ኤ340 የተሰኘው የግል አውሮፕላን ከዩናይትድ አረብ ኤሜሬትስ ወደ ኒካራግዋ እያቀና ነበር። አውሮፕላኑ ነዳጅ ለመቅዳት ባረፈበት ወቅት ነው ፖሊስ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ሰዎችን እያዘዋወረ ሊሆን ይችላል ሲል እንዳይንቀሳቀስ ያገተው።

276 ሰዎች ወደ ሕንድ ሲመለሱ ሁለት ሕፃናትን ጨምሮ 25 ሰዎች ፈረንሳይ ውስጥ ጥገኝነት ጠይቀው ቀርተዋል። ሁለት በሕገ-ወጥ ሰው ማዘዋወር የተጠረጠሩ ግለሰቦችም ለምርመራ ፈረንሳይ ውስጥ እንዲቆዩ ተደርገው ነበር። ነገር ግን ሁለቱ ሰዎች በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ነፃ እንዲወጡ ሆኗል።

ሌጀንድ ኤርላይንስ የተሰኘው ድርጅት ንብረት የሆነው አውሮፕላን በሙምባይ ሰዓት አቆጣጠር ከእኩለ ለሊት በኋላ ነው ያረፈው። ባለፈው ሐሙስ ነው ከፓሪስ 130 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከሚገኘው ሻሎን-ቫትሪ አየር ማረፊያ እንዳይንቀሳቀስ የታገደው።

ፖሊስ አውሮፕላኑ ውስጥ ካሉ ተሳፋሪዎች መካከል የተወሰኑት “የሕገ-ወጥ ዝውውር ሰለባ ናቸው” የሚል ጥቆማ ከደረሰው በኋላ ነው አውሮፕላኑ እንዳይንቀሳቀስ ያገደው። አውሮፕላኑ ውስጥ ከነበሩት አብዛኛዎቹ ዩኤኢ የሚሠሩ ሕንዳውያን መሆናቸው ይታመናል። አንድ ሶስተኛ ተሳፋሪዎች ደግሞ ከምዕራባዊቷ የሕንድ ግዛት ጉጃራት የመጡ መሆናቸው ተዘግቧል።

የፈረንሳይ ባለሥልጣናት እንደሚያምኑት ተሳፋሪዎቹ ወደ ኒካራግዋ እያቀኑ ያሉት ወደ ዩናይትድ ስቴትስ አሊያም ካናዳ ለመግባት አቅደው ስለነበር ነው። አውሮፕላኑ ወደ ሕንድ የተመለሰው ምንም ዓይነት ወንጀል ሳይፈፅም ስለቀረ ነው ወይ የሚለውን ጥያቄ ባለሥልጣናት እስካሁን አልመለሱም።

አውሮፕላኑ በዕቅዱ መሠረት ወደ ኒካራግዋ መሄድ ሲገባው ወደ ሙምባይ ለምን እንደተመለሰም ግልፅ አይደለም። ሌጀንድ አየር መንገድ የሮማንያ የግል አውሮፕላን ድርጅት ሲሆን አራት አውሮፕላኖች እንዳሉት ፍላይትራዳር የተሰኘው የበረራ ቁጥጥር ድረ-ገፅ ይጠቁማል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## የሱዳን ተፋላሚ ኃይሎች በጅቡቲ እንዲነጋገሩ መጋበዛቸው ተገለጸ

የሱዳን ተፋላሚ ኃይሎች በጅቡቲ እንዲነጋገሩ በደብዳቤ ተጋብዘዋል። የምስራቅ አፍሪካ የልማት ድርጅት ወይም ኢጋድ ሁለቱን የሱዳን ተፋላሚ ኃይሎች በጅቡቲ ለማወያየት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ባለፈው ሚያዝያ አጋማሽ ጀምሮ በሱዳን ጦር እና በፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች መካከል የተቀሰቀሰው ጦርነት 9ሺ ሰዎች እንዲገደሉ እና ከስድስት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች ደግሞ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ስደተኞች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።



የተለያዩ ሚዲያዎች እንደዘገቡት የሱዳን ጦር መሪ እና የሉዓላዊ የሽግግር ምክርቤቱ ፕሬዝደንት ጀነራል አልቡርሃን በጅቡቲ ከመሀመድ ደጋሎ ወይም ሄሜቲ ጋር በሚቀጥለው ሀሙስ እንዲገኙ በኢጋድ ኃላፊ የግብዣ ደብዳቤ ተጽፎላቸዋል። ውይይቱ ስለተኩስ አቁም እና የሰብዓዊ ርዳታ መንገድ ክፍት ስለሚደረግበት ሁኔታ ሊያተኩር እንደሚችል የዲፕሎማት ምንጮች ተናግረዋል።

ይህ ስብሰባ የሚካሄድ ከሆነ ጦርነቱ ከተጀመረበት ከባለፈው ሚያዝያ ወር በኋላ በቡርሃን እና በሄሜቲ መካከል የተደረገ የመጀመሪያው ይሆናል። እነዚሁ ምንጮች እንደሚሉት ስብሰባው ጦርነቱ ቆሞ የፖለቲካ መፍትሄ በሚመጣበት ሁኔታዎች ላይ ይመከራል።

ስብሰባው እንዲካሄድ እቅድ የተያዘው ከኢጋድ እና ከአፍሪካ ህብረት በተጨማሪ በአሜሪካ እና በሌሎች ሀገራት ጫና መሆኑን ምንጮቹ ገልጸዋል። ሱዳንን ለሶስት አስርት ዓመታት የመሩት አመር ሀሰን አልበሽር በሕዝባዊ አመጽ ከሥልጣን ከወረዱ በኋላ በሱዳን በጠቅላይ ሚኒስትር ሀምዶክ የሚመራ የሲቪል አስተዳደር ተቋቁሞ ነበር። ነገርግን የሱዳን ጦር ጀነራሎች በጠቅላይ ሚኒስትር ሀምዶክ አስተዳደር ላይ መፈንቅለ መንግሥት አድርገው ሥልጣን በብቸኝነት ተቆጣጠሩ።

ወታደራዊ ሥልጣን ያየዙት ጀነራል ቡርሃን እና ሄሜቲ በመካከላቸው ግጭት ተቀስቅሶ፣ ሀገሪቱ ቀውስ ውስጥ ገብታለች ሲል አል ዐይን ዘግቧል። አሁን ሱዳንን ከባድ ቀውስ ውስጥ የከተታት ግጭት የተቀሰቀሰው በሥልጣን ሽኩቻ ውስጥ በቆዩት የሀገሪቱን ሉዓላዊ የሽግግር መንግሥትን በዋናነት እና በምክትልነት ሲመሩ በቆዩት የጦር ኃይሎቹ አዛዥ ጄኔራል አብደል ፋታህ አል ቡርሐን እና የፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ አዛዥ ጄኔራል ሞሐመድ ሐምዳን ዳጋሎ በሚመሯቸው ወታደሮች መካከል ነው።

ለቀናት ከቆየ ውጥረት በኋላ የፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ አባላቱን በተለያዩ የሱዳን አካባቢዎች ማሰማራቱን ተከትሎ የሀገሪቱ ጦር ሠራዊት አዛዦች ስጋት ውስጥ በመግባታቸው ነበር በሁለቱ ኃይሎች መካከል ካርቱም ውስጥ ግጭቱ ሚያዚያ 07/2015 ዓ.ም. የተቀሰቀሰው።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## የመጀመሪያ የአማርኛ ቴሌፕሪንተር ፈጣሪ ኢንጂነር

-ኢንጂነር ተረፈ ራስወርቅ

ክብረዓብ በላቸው

አብዛኞች እንደዋዛ ጥለዋት በሚለይዋት ዓለም በተቃራኒው ጥቂቶች ከራሳቸው ለሌሎች የሚተርፍ አስተዋፅዖ አበርክተው ማለፉ ይሳካላቸዋል። በሚያልፍ ዕድሜ የማያልፍ ሥራ ሠርተው ስማቸው ሲወሳ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል የአማርኛ ቴሌፕሪንተር ፈጣሪው ኢንጂነር ተረፈ ራስወርቅ አንዱ ናቸው።

ኢንጂነር ተረፈ ራስ ወርቅ፣ መጋቢት 2 ቀን 1928 ዓ.ም በአንኮበር ውስጥ በምትገኝ አፈርባይኔ በምትባል መንደር ከአባታቸው ከመምህር ራስወርቅ ወልደመስቀልና ከእናታቸው ከወይዘሮ አስካለ ማሪያም ገ/ጊዮርጊስ ተወለዱ።

ኢንጂነር ተረፈ የተወለዱት ውጥንቅጥና ቀውጢ ጊዜ በነበረበት የጣሊያን ወረራ ወቅት ነበር። ረቡዕ መጋቢት 2 ቀን 1928 ዓ.ም። እናታቸው አራስ ቤት ሆነው ሕጻኑን ተረፈን ሲንከባከቡ በድንገት የጠላት ጣሊያን አውሮፕላኖች አንኮበር ላይ የቦምብ ዝናብ ይጥላሉ። በአካባቢው የነበሩት የሳር ክዳን ቤቶች እንደችቦ ይቀጣጠላሉ። ሕዝቡም ነፍሴ አውጭኝ ብሎ ይሯሯጣል፤ ከጥቃቱ በኋላ እሳቱ ይጠፋል።

የተረፈው ሰውም እየፈራ ወደቀዬው ይመለሳል። ነገር ግን የያኔው ሕጻን ተረፈና ወላጅ እናቱ የደረሱበት አልታወቀም ነበር። ሞተዋል ተብሎ ለቅሶ ይጀመራል። አባታቸው መምህር ራስወርቅም ወዲያና ወዲህ ፈልጉ እያሉ ይወራጫሉ። በማግስቱ ረፋድ ሲል ሁሉም እረጭ ሲል ወላጅ እናቱ ሕጻን ተረፈን በጉያቸው አቅፈው ከተደበቁበት ዋሻ ወጥተው ወደመንደራቸው ሲመለሱ በሕይወት በመገኘታቸውን እልልታ ሆነ። መምህር ራስወርቅም ልጄ ተረፈልኝ ብለው እግዚአብሔርን አመስግነው ለልጃቸው ተረፈ ብለው ስም አወጡለት።

ኢንጂነር ተረፈ ፊደል የቆጠሩት አንኮበር ወላጅ አባታቸው ጋር ሆነው ነበር። የጣሊያን ጦር እንደወጣ በ1933 ዓ.ም የኢንጂነር ቤተሰብ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ። የያኔው ታዳጊ ተረፈም አንድ ቄስ ትምህርት ቤት ገብተው ዳዊት ደግመዋል። ከዚያም ለአንድ ዓመት ዳግማዊ ምኒሊክ ትምህርት ቤት ተላኩና የአንደኛ ክፍል ትምህርት አጠናቀው ወደ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ተዛወሩ።

ኢንጂነር ተረፈ፣ ተፈሪ መኮንን ተማሪ ቤትን በጣም ወደዱት ምክንያቱም ቤታቸውና ትምህርት ቤቱን አንድ አጥር ነበር የሚለየው። በዘመኑ በአገሩ ውስጥ ትልቅ ከሚባሉት ትምህርት ቤቶች አንዱ ነበር። ከአንድ ሺህ ተማሪዎች በላይ ነበሩት። የንጉሠ ነገሥቱ ቤተ መንግሥት ቅርብ ስለነበር ጃንሆይ በየጊዜው እነ ኢንጂነር ተረፈን ይጎበኙ ነበር። ይህም ዘወትራዊ ጉብኝት ተማሪዎቹንና መምህራኑን ያስደስታቸውና ያበረታታቸው ነበር።

በወቅቱ ከኢትዮጵያውያን አስተማሪዎች ጋር የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪና መምህራኖቹ ከካናዳ የመጡ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ኢየሱሳውያን የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ነበሩ። ከሦስተኛ ክፍል ጀምሮ ታዳጊ ተረፈን የሚያስተምሩት የውጭ አገር ተወላጅ አስተማሪዎች ነበሩ።

በመስከረም ወር 1947 ዓ.ም ኢንጂነር ተረፈ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ደጅ ረገጡ። ስማቸውን በሳይንስ ክፍል ሲያስመዘግቡ ሰው ሁሉ አብደሃል ወይ ብሎ ታዘባቸው። ምክንያቱም ከተፈሪ መኮንን የሚመጡ ልጆች እንደሌሎቹ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ንጹሕ ኬሚስትሪና ንጹሕን ፊዚክስ በመውሰድ ፈንታ ጠቅላላ ሳይንስ ስለሚማሩ የኮሌጅ ሳይንስ ይከብዳቸዋል ይባል ስለነበረ ነው።

እንደአጋጣሚ ሆኖ ኢንጂነር ኮሌጅ ውስጥ እንደገቡ የመጀመሪያው የኬሚስትሪ ፈተና በጣም ቀላል ስለ ነበረ ውጤቱ ሲለቀቅ ዘጠና ዘጠኝ ከመቶ አገኙ። ይህ ውጤት ግሩም ተባለ። ወሬውም ወደ ቲኤምኤስ ተዛመተ። ኢንጂነር ተረፈም፣ የእችላለሁ መንፈስ ውስጣቸው ስላደረ የትምህርት ዘመናቸውን ያለችግርና በራስ መተማመን ለማለፍ ችለዋል።

ኢንጂነር ተረፈ፣ ኮሌጁ ውስጥ ሳሉ በብዙ ተጓዳኝ ሥራዎች ውስጥ ተካፋይ ነበሩ። የኮሌጁ የሶፍት ቦል ቲም ካፒቴን ነበሩ። እንዲሁም በጥንታዊ ባሕላዊ ማኅበረ ጥናት ላይም ይካፈሉ ነበር።

ለሀገራቸው እና ለታሪክ ታላቅ ፍቅር የነበራቸው ኢንጂነር ተረፈ ራስወርቅ ከ100 ዓመት አስቀድሞ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በቤተመንግሥትነት ይጠቀሙበት የነበረውን የአንኮበር ቤተ-መንግሥትን፣ አንኮበር ሎጂ ብለው የቀድሞ ታሪኩን በጠበቀ መልኩ አሳድሰው ዘመን ተሻጋሪ ቅርስ ያኖሩ ናቸው፡፡ ይህም የበርካታ ቱሪስቶች መስሕብ መሆን የቻለ ነው

ከዚህ ጋር ተያይዞ በ1949 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቲያትር ንጉሠ ነገሥቱ በሚገኙበት ለሀገራችን የትኛው ትምህርት ይበልጥ ይበጃል? በሚል ርዕስ ኮሌጁ አንድ የአደባባይ ሙግት አዘጋጅቶ ነበር። ሙግቱም ለሀገራችን በጣም የሚጠቅመው ትምህርት ሕግ ወይስ ሕክምና ወይስ መሐንዲስነት ወዘተ የሚል ነበር። ኢንጂነር መሐንዲስነት ነው የሚለውን መስመር ሲይዙ ተስፋዬ ገሠሠ ሕግ ይሻላል ብሎ ተነሳ። ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ደግሞ አስተማሪነት ይበልጣል ብሎ ተከራከረ። ኢንጂነር አንደኛው መከራከሪያቸው ለመሐንዲስ ሥራ የሚያስፈልጉትን የደን ውጤቶች መንከባከብ ያስፈልጋል የሚል ሲሆን የሚገርመው ግርማዊነታቸው ተረፈ ሲናገር ማስታወሻ ይወስዱ እንደነበር ይነገራል።

በወቅቱ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በሳይንስ ዘርፍ ሙሉ የዲግሪ ፕሮግራም ስላልነበረው ከ 3 ዓመት ትምህርት በኋላ በመንግሥት ወደ ውጭ ሀገር ተማሪዎች ይላኩ ነበር። በዚህም መሠረት፣ ኢንጂነር ተረፈ ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር ወደ ሬንስለር ፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት ወደ ትሮይ ኒውዮርክ ስቴት ተላኩ።

በነበረው ልማድ መሠረት ተማሪዎች ወደውጭ ሀገር ሲላኩ ንጉሠ ነገሥቱ ጋር ቀርበው መሰናበትና አባታዊ ምክር ይሰጣቸው ነበር። ተሰናባች ተማሪዎች ንጉሡን የተሰናበቱት በደብረ ዘይት ቤተ መንግሥታቸው ነበር። ጃንሆይም ጥሩ አቀባበል ካደረጉ በኋላ ሀገራችሁን ተመልሳችሁ አገልግሉ ሲሉ አደራ ሰጡ።



በ1950 ዓ.ም ነሐሴ ወር ኢንጂነር አዲስ አበባን ለቅቀው ወደ አሜሪካ ለመሄድ ተነሱ። በመጀመሪያ ኢንጂነርና ጓደኛቸው ማህዲ በኤሌክትሪክ መሐንዲስነት መማሪያ ዋና ክፍል ተመዘገቡ። ትምህርቱም በጣም ከባድ ሆኖ አገኙት። ነገር ግን እጅ ባለመስጠት ጠንክረው በመማር በ1952 ዓ.ም የተሰጣቸውን ክፍል ትምህርት ጨርሰው በኤሌክትሪክ ምሕንድስና የመጀመሪያ ዲግሪ ተቀብለው ወደ ሀገር ቤት ተመለሱ።

ኢንጂኒየር ተረፈ ከውጭ እንደተመለሱ የመጀመሪያ ሥራቸውን ቴሌ ውስጥ ጀመሩ። ሥራውንም እንደጀመሩ ሁሉንም ክፍሎች በሚገባ እንዲጎበኙ ነበር የተደረገው። ከባሕር ማዶም እንደመጡ በሙያቸው ከፍተኛ ተሰሚነት ነበራቸውና፤ የነበሩትን ክፍሎች ከጎበኙ በኋላ የትራንስሚሽንና የረጂም ርቀት ስርጭት ከሚባል ክፍል በኃላፊነት ተመደቡ። የ25 ዓመት ወጣት ሳሉ ቴሌ ውስጥ ትልቅ የሚባል ኃላፊነት ተሰጣቸው። የእድሜ ማነስ አንድም ተፅዕኖ ሳይፈጥርባቸው ሥራቸውን በአግባቡ ሊወጡ ይሞክሩ ነበር። በዛን ጊዜ የነበሩት ስዊዲኖች አንድን ሰው የሚመዝኑት በእድሜው ሳይሆን በሥራ ብቃቱና በአመለካከት ብስለቱ ነበር።

እርሳቸው ከውጭ መጥተው ቴሌ በሚሠሩበት ጊዜ የፋክስ ግንኙነት አልነበረም። አብዛኛው መልዕክት ይተላለፍ የነበረው በቴሌግራፍ ነበር። ኢንጂኒየር ተረፈ ለአንድ የሀገር ውስጥ ሚዲያ ሁኔታውን ሲገልጹ “እንዲህ ነበር ያሉት... በጣም የደነቀኝ የዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ቋንቋ የሚላክ ቴሌግራም ሁሉ በላቲን ፊደል ነበር የሚፃፈው። ለምሳሌ ‘እመጣለሁ’ ለማለት ሲፈለግ emetalehu ተብሎ ነበር የሚጻፈው። ” “እንዴት የራሳችን ፊደል እያለን በላቲን ፊደል ይጻፋል ስል ለራሴ ጥያቄ አቀረብኩ። ለምን በራሳችን ፊደል መጻፍ አልተቻለም? የሚል ጥያቄ ባነሳም አበረታች መልስ አላገኘሁም። ‘ፈጽሞ አይቻልም፤ ብዙ ሰዎች ሞክረው ትተውታል’ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ነበር የገጠመኝ። በኋላም አሊቬቲ የተባለ ኩባንያ የአማርኛ ቴሌፕሪንተርን ለመሥራት ሞክሮ አልቻለም ሲሉ ሌላ መረጃ አቀበሉኝ። እኔም ‘በኢትዮጵያ ፊደል ቴሌፕሪንተር’ ሊኖር አይችልም የሚባለውን ተስፋቢስ ዜና ልቀበለው አልቻልኩም። ” ይላሉ።

በዚህም መነሻ ኢንጂነር ተረፈ የአማርኛ ቴሌፕሪንተር ለመሥራት ተነሳስተው ምርምሩን ጀመሩ። በወቅቱ ፕሪንተሮቹ ለላቲን ፊደል ነው የተፈጠሩት የሚል ግትር መከራከሪያ ተነስቶ ነበር። እንደሚታወቀው የላቲን ፊደል 26 ነው። የአማርኛ ደግሞ 270 ነው። ታዲያ የመከራከሪያ ሃሳቡ ፕሪንተሩ ለ270 ፊደላት ቦታ የለውም የሚል ነበር።

ኢንጂነሩ፣ ይህን ሃሳብ ጊዜ ሰጥተው ምርምሩን ቀጠሉበት። ኢንጂነር ተረፈ ያደረጉት ዋናው ጥናትም የኢትዮጵያን ፊደሎች እንዴት ቴሌፕሪንተር ውስጥ ማስገባት ይቻላል የሚል ነበር። ኢንጂነሩ ያኔ ለማስተዋል እንደሞከሩት የኢትዮጵያ ፊደሎች ቅርጽና ውበት እጅግ የሚያስደንቅ ነው። በብዛት 270 ቢሆኑም፣ ቅርጻቸው ግን ከ20 አይበልጥም።

ያኔ እርሳቸው ለማቅረብ እንደሞከሩት የላቲን ፊደሎች 26 ይባሉ እንጂ “ካፒታል ሌተር፤ ስሞል ሌተር” ሲባል ወደ አርባ ይጠጋሉ። የእኛ ግን ይላሉ የያኔው ወጣት ተመራማሪ “ቅርጹ ሲታይ በጣም ተመሳሳይ ነው። ለምሳሌ ‘ሀ’ ሲገለበጥ ‘በ’ ይሆናል። በአናቱ ላይ ዘንግ ሲደረግበት ‘ሰ’ ይሆናል። ‘ሰ’ ላይ መስመር ሲደረግበት ‘ሸ’ ይሆናል። ” በማለት ጥናታዊ ምርምሩን አጠናክረው ቀጠሉ።

እነዚህን ቅርጾች በማስተካከል ብቻ ቴሌፕሪንተሩን መሥራት እንደሚቻል ኢንጂነር ተረፈ በምርምር ማረጋገጥ ቻሉ። ከዚህ በኋላ የዚያን ዘመን ቴሌፕሪንተር የፊደላት ድርድር (ኪቦርድ) ቅርጽ ማስተካከል ያዙ። ማሽኑ ላይ የሚቀረጹት ፊደሎች ቁመታቸውና አቀማመጣቸው ወረቀቱ ላይ የቱ ጋር እንደሚቀመጡ በደንብ ካስተካከሉ በኋላ ሲጻፍ ፈጽሞ እንደማያስቸግር በሚገባ አረጋገጡ።

የኪቦርዱን ቅርጽ ካስተካከሉት በኋላ በጊዜው የአዕምሯዊ ንብረት ሕግ የፈጠራ ውጤታቸውን በይፋ አስመዘገቡ። በኋላም፣ ሶፍትዌሩን ሲመንስ ለሚባለው የጀርመን ኩባንያ አስረከቡ። በ1960 ዓ.ም (ቴሌፕሪንተሩ) የአማርኛ ፊደል ይዞ ሀገር ቤት ሲመጣ ልዩ ስሜትና የሥራ ተነሳሽነት ተሰማቸው።

ወዲያው፣ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ቴሌፕሪንተሩን መረቁ። በምረቃው ዕለት አንዱ ቴሌፕሪንተር አሥመራ ቤተ-መንግሥት ተደረገ። አንደኛው አዲስ አበባ ተቀመጠ። በወቅቱ የኤርትራው ገዢ ራስ አሥራተ ካሣ በአዲሱ መኪና መልዕክት ወደ አዲስ አበባ ሲልኩ ግርማዊነታቸው መልዕክቱን አይተው የደስታ ስሜታቸውን መደበቅ አልተቻላቸውም ነበር።

የዓለም አቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን አንድነት በ1865 ዓ.ም የተፈጠረ መቀመጫውን ጄኔቭ ያደረገ ትልቅ ድርጅት ነው። ይህ ድርጅት ኢንጂነር በሄዱበት ዘመን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አንድ ክፍል ነበር። ያኔ የኅብረቱ ዋና ጸሐፊ የቱኒዚያው ሚስተር መሐመድ ሚሊ ነበሩ። ኅብረቱ ሰዎችን ሊቀጥር ሲያወዳድር የአፍሪካ ክፍል ክፍት ሲሆንባቸው ለአባል ሀገሮች ሁሉ ክፍት ቦታ መኖሩን አሳወቁ። ኢንጂኒየርም ያኔ ነበር ከተወዳዳሪዎቹ አንዱ ለመሆን የበቁት። የትምህርት ሁኔታውና የሠሩት ሁሉ በሚገባ ታይቶ የኅብረቱ ባልደረባ ሊሆኑ ቻሉ። ከዛም በዓለም አቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ኅብረት የአፍሪካ ጉዳይ ክፍል ውስጥ ማገልገል ያዙ። በጄኔቭ አንድ ብለው የጀመሩት የሥራ ዘመን ለ40 ዓመታት ዘለቋል።

በኅብረቱ ውስጥ የአፍሪካ ጉዳዮች ኃላፊ ሆነው በሠሩባቸው ዓመታት የአፍሪካን የቴሌኮም ዕድገት ዕውን ለማድረግ የአቅማቸውን ያህል ሞክረዋል። የመጀመሪያው የኅብረቱ ቀዳሚ ተግባር የቴሌኮሙኒኬሽን ማሠልጠኛዎች በየሀገሩ መመሥረት ነበር። በዚህ መሥሪያ ቤት በነበራቸው ቆይታ የበርካታ ሀገራትን የቴሌኮም የዕድገት ደረጃ ለመለየት ችለዋል።

ለሀገራቸው እና ለታሪክ ታላቅ ፍቅር የነበራቸው ኢንጂነር ተረፈ ራስወርቅ ከ100 ዓመት አስቀድሞ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በቤተመንግሥትነት ይጠቀሙበት የነበረውን የአንኮበር ቤተ-መንግሥትን፣ አንኮበር ሎጂ ብለው የቀድሞ ታሪኩን በጠበቀ መልኩ አሳድሰው ዘመን ተሻጋሪ ቅርስ ያኖሩ ናቸው። ይህም የበርካታ ቱሪስቶች መስሕብ መሆን የቻለ ነው።

ኢንጂነር ተረፈ በ1980ዎቹ መጀመሪያ ለዓለም አቀፉ የቴሌኮሙኒኬሽን ኅብረት ዳይሬክተርነት ለመወዳደር በእጩነት የቀረቡ ታላቅ ሰው ነበሩ። በተለይ ሀገራችን በቴሌኮም ዘርፍ ተጠቃሚ እንድትሆን ልምድና እውቀታቸውን ሲያካፍሉ፤ ምክር ሲለግሱ የነበሩ ናቸው።

በ1954 ዓ.ም ከወይዘሮ ብርሀኔ አስፋው ጋር በጋብቻ የተጣመሩት ኢንጂነር ተረፈ ራስወርቅ፤ በትዳራቸው 3 ልጆችን እንዲሁም የልጅ ልጆችን አፍርተዋል። ከኢትዮጵያ ባለፈ በዓለም አቀፍ የቴሌኮም ባለሙያዎች ዘንድ በክብር የሚነሱት እኚህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ በተወለዱ በ86 ዓመታቸው ሚያዝያ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ከዚህ ዓለም ድካም አርፈዋል።

ኢንጂነር ተረፈ በሕይወት ዘመናቸው ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን በታታሪነትና በጥልቅ ሀገራዊ ፍቅር በማገልገል ታላቅ አስተዋፅዖ ያበረከቱ ሰው ነበሩ። እኛም እኚህን የሀገር ባለውለታ ነፍስ ይማር እንላለን።

# ስፖርት

## ባምላክ ተሰማ የአፍሪካ ዋንጫ ጨዋታዎችን በዋና ዳኝነት ይመራል

ዓስማየሁ ግዛው

34ኛው የአፍሪካ ዋንጫ በኮትዲቫር አስተናጋጅነት ሊጀመር ዛሬ አስራ ሰባት ቀን ቀርቶታል። የስፖርቱ ዓለም መገናኛ ብዙሃንም ትኩረታቸውን በዚሁ የ2023 አፍሪካ ዋንጫ ላይ ማድረግ ጀምረዋል። የውድድሩ አዘጋጆችም በርካታ ቅድመ ዝግጅቶችን በማድረግ፣ የውድድሩን መጀመር በጉጉት እየተጠባበቁ ይገኛሉ።

ከቅድመ ዝግጅቶቹ መካከል ውድድሩን የሚመሩትን ዳኞችና ባለሙያዎችን የመለየት ሥራ አንዱ ነው። በዚህም መሠረት የአፍሪካ እግር ኳስ ኮምፌዴሬሽን (ካፍ) ሰሞኑን ውድድሩን የሚመሩትን ዳኞችን ይፋ አድርጓል። ኢትዮጵያዊው ኢንተርናሽናል አርቢትር ባምላክ ተሰማ የዘንድሮውን የአፍሪካ ዋንጫ ከሚመሩ ዳኞች ዝርዝር ውስጥ መካተቱ ታውቋል።

በአፍሪካ አንጋፋና ስመ ጥር ከሆኑ የእግር ኳስ ደኞች ውስጥ አንዱ የሆነው ኢንተርናሽናል ዳኛ ባምላክ ተሰማ ዘንድሮ የአህጉሪቱን ታላቅ የእግር ኳስ ውድድር ለመምራት ከኢትዮጵያ በብቸኝነት እንደተወከለ ተረጋግጧል። ባምላክ ኢትዮጵያ ከምትኮራባቸው ዓለም አቀፍ ዋና ዳኞች ውስጥ አንዱ ሲሆን በበርካታ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ኢትዮጵያን በመወከል ብቃቱን ማሳየት ችሏል። አርቢትሩ ቆፍጣናና ጨዋታዎችን ሲመራ ባለው የራስ መተማመን እና ያመነበትን ውሳኔ ለመወሰን ወደ ኋላ የማይል መሆኑን ባለፈው የካሜሩን አፍሪካ ዋንጫ ላይ ይበልጥ በማሳየት አድናቆት ማትረፉ ይታወሳል።

ይሄ በራስ መተማመኑ እና ከፍተኛ የሆነ ልምዱም ካፍ ዘንድሮም ውድድሩን በኮትዲቯር፣ ከሚመሩት ዳኞች ብቸኛው ኢትዮጵያዊ ዋና ዳኛ አድርጎ እንዲመርጠው አድርጓል። የእሱ መመረጥ ኢትዮጵያ ብቻም ሳትሆን የአፍሪካ እግር ኳስ ኮምፌዴሬሽን ከሚተማመንባቸውና ዳኞች ውስጥ አንዱ መሆኑን በድጋሚ ያረጋገጠበት ነው። ለዚህ እንዲበቃ ያደረገው ጉዳይ ደግሞ በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ ውድድሮች ወጥነት ባለው መልኩ ጨዋታዎችን የመምራት ብቃት ማሳየት በመቻሉ ነው። ኢትዮጵያ በዘንድሮ ውድድር እንደማትሳተፍ የሚታወቅ ሲሆን በዳኝነቱ ግን ኢንተርናሽናል ዋና ዳኛ ባምላክ ተሰማ የሚወክላት ይሆናል።

ባምላክ የእግር ኳስ ዳኝነቱን ዓለም አንድ ብሎ የጀመረው እአአ በ2003 ሲሆን በ2009 የፊ (FIFA) ዳኛ መሆን ችሏል። በ2010 ጂቡቲ ከሶማሊያ ያደረጉትን ጨዋታ በመምራት የመጀመርያውን ዓለም አቀፍ ተሳትፎውንም ጀምሯል። በዚሁ ዓመት የሴካፋ (CECAFA) ውድድር ሲካሄድ ንቁ የሆነ ተሳትፎን በማድረግ እስከ ፍጻሜ ድረስ 5 ጨዋታዎችን መርቷል። በ2011 የሴካፋ ውድድር እንደዚሁ አራት ጨዋታዎችን መርቷል። በ2012 ታንዛኒያ በተካሄደ የክለቦች ቻምፒዮንስ ሊግ ውድድር የመጀመርያውን ዙር በመምራት ግስጋሴውን ቀጥሏል። በተጨማሪም ግብፅ የተካሄደውን ሁለተኛ ዙር የክለቦች ኮምፌዴሬሽን ጨዋታንም መምራት ችሏል።

የአፍሪካ ዋንጫንም በብቃት መምራት እንደሚችል በተደጋጋሚ ያስመሰከረው ኢትዮጵያዊ አርቢትር በ2022 በሴኔጋልና ቡርኪና ፋሶ መካከል



ኢንተርናሽናል አርቢትር ባምላክ ተሰማ፣

የተካሄደውን የግማሽ ፍጻሜ ጨዋታ ተቆጣጥሮ በመምራት ብዙዎችን አስደምሟል። በወቅቱ የፍጹም ቅጣት ምት የሚያሰጡ የሚመስሉትን ጥፋቶች ተመልክቶ የቫርን ውሳኔ ስላላመነበት፤ ለሁለቱንም ጥፋቶች ፍጹም ቅጣት ሳይሰጥ ቀርቷል።

በ2009 የፊፋ ዋና ዳኛ መሆን የቻለው ባምላክ ለ2014 የዓለም ዋንጫ የተካሄዱትን የመጀመርያ ዙር ማጣሪያ ጨዋታዎችን በመምራት ሥራውን የጀመረ ሲሆን ጂቡቲ እና ናሚቢያ ያካሄዱትን ጨዋታ መርቷል። በ2018 በራሺያ አስተናጋጅነት በተካሄደው የዓለም ዋንጫም አፍሪካን በመወከል ከተመረጡት 6 ዋና ዳኞች አንዱ ነበር።

ከጥር 4 እስከ የካቲት 3 በኮትዲቫር አስተናጋጅነት በሚካሄደው የዘንድሮ የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ጨዋታዎችን ከሚመሩት ዋና ዳኞች አንዱ ባምላክ ተሰማ እንደሆነም ካፍ ከቀናት በፊት ይፋ ባደረገው ዝርዝር አሳውቋል። ለዚህ ትልቅ የአህጉሪቱ ውድድር 68 ከፍተኛ ልምድና ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ያካተተው ካፍ በቅርቡ የአካል ብቃትና ሌሎች የሚያስፈልጉ መመዘኛዎችን በመስጠት የሚያዘጋጃቸው ይሆናል። የተመረጡት ዳኞች በሙሉ እአአ ጥር 5 2024 ኮትዲቯር ይደርሳሉ የተባለ ሲሆን የማነቃቂያ ሥልጠናዎችን በመውሰድ ውድድሩን ይመራሉ።

ተጠባቂውን ውድድር በዋና ዳኝነት ለመምራት ከአህጉሪቱ ሁሉም ክፍል በዋና፣ በረዳት፣ በቫር ዳኝነት የተካተቱ ሲሆን ባምላክን ጨምሮ 26 ዋና ዳኞች ውድድሩን ለመምራት ተመርጠዋል። በተጨማሪም 30 ረዳት ዳኞችና 12 የቫር ዳኞች ውድድሩን ለመምራት ከወዲሁ ተለይተው ተካተዋል።